# ፀረ-ሙስና

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ቅፅ 01 ቁጥር 19 ጥር 30/2016 ዓ.ም


## በውስጥ ገፆች

- ኮሚሽኑ ከአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ፣
- በመዲናዋ በሙስና መከላከል ሥራ ከ 876 ነጥብ 9 ሚሊየን ብር በላይ ማዳን መቻሉ ተገለጸ፣
- በፍርድ ቤት ያላቸውን ክርክር ለማሸነፍ ለዳኛ ጉቦ ሲሰጡ የነበሩ ወንድማማቾች በእስራት ተቀጡ፣

## ሕገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመግታት ከሐሳብ የዘለለ ዓለም አቀፍ ትብብር የለም

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)





ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በ6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 14ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ከሙስና እና ከሕገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ጋር በተያያዘ ከምክር ቤት አባላት ለተነሳላቸው ጥያቄ ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት ሕገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር በጣም ትልቅ ችግር እንደሆነና በጉዳዩ ላይም በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አንስተዋል፡፡

የቴክኖሎጂውን ዘርፍ እና የባንክ አሠራርን ከማዘመን አንፃር የሪፎርም ሥራዎች ቢከናወኑም አሁንም ችግሩ መኖሩን ጠቅሰዋል፡፡ምክንያቶችን ተገን በማድረግ መንግሥት ገንዘብ ከሀገር አያሸሽም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ÷ መንግስት ያገኘውን ገንዘብ ሁሉ በሀገር ውስጥ ልማት ላይ እያዋለ ነው ብለዋል፡፡ የሚታዩ ልማቶችም የዚህ ውጤት ማሳያ መሆናቸውን ነው ያስገነዘቡት፡፡


ይሁን እንጂ ግለሰቦች ባላቸው ግንኙነትና የተለያየ ስልት ተጠቅመው ገንዘብ የማዘዋወር ሥራቸውን እንዳላቆሙ ጠቁመው÷ ይህንን ተግባር ለመከላከል ተጨማሪ ሥራዎችን ማከናወን እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል፡፡ ዓለም ስለ ሙስና ሲያብራራ፣ አፍሪካ እንዴት በሙስና ውስጥ እንደተዘፈቀች ሲገልፅ እና ሙስና እንዴት ፀረ ልማት እንደሆነ ሲተነትን እንጂ ከሙስና ጋር አልተባበርም ሲል አይተው እንደማያውቁም ገልፀዋል፡፡ ከማብራሪያ ባለፈም የሚሰረቀው ሁሉ ገንዘብ ወደ ተለያዩ ሀገራት ሲወሰድ ከየት እንደመጣ እየታወቀ ይህ የሌብነት ገንዘብ ነው ብሎ ለመመለስ ትብብር ሲደረግ እንደማይታይም ጠቁመዋል፡፡ በመሆኑም ትብብሩ ከሐሳብ በዘለለ ወደ ተግባር የገባ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ እስከ አሁን የታየ ለውጥ አለመኖሩን አያይዘው ገልጸዋል፡፡

## የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ሲያጭበረብሩ የነበሩ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር ዋሉ

ልዩ ልዩ ሐሰተኛ ሰነዶችንና ዘዴዎችን በመጠቀም ህብረተሰቡን ሲያጭበረብሩና ሲያታልሉ የነበሩ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን የፌዴራል ፖሊስ አስታወቀ፡፡

ተጠርጣሪዎቹ የመንግስት ባለስልጣናትን ስም በማንሳት "እነ እከሌን እናውቃለን፤ ጉዳያችሁን እንጨርስላችኋለን" በማለት የተለያዩ ሰዎችን በማጭበርበር ገንዘብ እየተቀበሉ ባሉበት ወቅት ከማስረጃ ጋር በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ ተጠርጣሪዎቹ ባለሃብትና ከፍተኛ



ገንዘብ እንዳላቸው ለማስመሰል በርካታ የአሜሪካን ዶላር በሳምሶናይት ይዘው ፎቶግራፍ በመነሳት እና እራሳቸውን በማሳየት ሲያጨብረብሩ መቆታቸው ተመላክቷል፡፡ በተጨማሪም የመከላከያ ሠራዊት እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት መሥሪያ ቤት የስራ ባልደረባ አባል ነን በሚል በሐሰተኛ መታወቂያ ህብረተሰቡን ሲያጭበረብሩና ሲያታልሉ እንደቆዩ ፖሊስ ገልጿል፡፡ ፖሊስ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 አካባቢ በሚገኘው የአንደኛው ተጠርጣሪ ሞቲማ ደለሳ ቦሮቃ መኖሪያ ቤት ውስጥ ባደረገው ብርበራ ለወንጀል ተግባር ማስፈፀሚያ የሚገለገሉበት 90 ሺህ ብር፣ አንድ ሽጉጥ ከ24 መሠል ጥይቶች እና ከ2 ካዝና ጋር፣ አይፎንና ሳምሳንግ ሞባይል፣ አንድ አፒድ ላፕቶፕ እና ሦስት ፍላሾች ተይዘዋል፡፡ ህብረተሰቡ በተመሳሳይ የወንጀል ተግባር የተሰማሩ ግለሰቦችንና ቡድኖችን በሚመለከትበት ጊዜ በማጋለጥ እና አሳልፎ ለፖሊስ በመስጠት እንዲተባበር የፌዴራል ፖሊስ ጥሪውን አቅርቧል፡፡

# የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ





የመግባቢያ ስምምነቱ በኢትዮጵያ የመሪዎች ሥነምግባራዊ መሪነት ላይ የአቅም ግንባታ፣ የምዘና እና አገርዓቀፍ የዕውቅና እንዲሁም የሽልማት ሥራዎችን በጋራ ለመሥራት የሚያስችል መሆኑ ተገልጿል፡፡

በስምምነት መድረኩ ንግግር ያደረጉት የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ፕሬዚዳንት አቶ ዛዲግ አብርሃ የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ዓላማው አመራሩ ሥነምግባርና ኢንተገሪቲ ኑሮት ለሀገር ጥሩ ሥራ እንዲሰራ የሚያደርግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በዚህም ማዕከሉ በተለያዩ ጉዳዮችና ተቋማት የመሰረተ ልማት ቅንጅት ይፈጥራል ብለዋል፡፡ ከፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋርም በሀገራችን በአመራሩ ሥነምግባርና ኢንተግሪቲ ላይ ሀሳብ እንዲይዝ በጋራ እንሰራለን ሲሉ ተናግረዋል፡፡ ማዕከሉ ሀገራት ሥነምግባርንና ኢንተገሪቲን ማዕከል የሚያደርጉበት ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፣ ይህን ማዕከል አድርገው የማይሰሩ አመራሮች ጥሩ ተግባር ስለማያከናውኑ ይህን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ አጽንኦት ሰጥተዋል፡፡ አመራሩ ሥነምግባር እንዲኖረው ሥልጠና እየሰጠን እና ጥሩ ሥነምግባር ያላቸው አመራሮችን ደግሞ እውቅና እና ሽልማት በመስጠት ሀገራችን በፀረ-ሙስና ትግል የምታደርገውን አስተዋጸኦ ለማጠናከር ከኮሚሽኑ ጋር አብረን እንሰራለን ብለዋል፡፡ መንግስትም ሙስናን በመታገል በኩል የሚያደርገው ጥረት የሚበረታታ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) በበኩላቸው የስምምነቱ ዓላማ በመንግስት ተቋማት፣ በህዝባዊ ድርጅቶች እና በልማት ድርጅቶች ያሉ አመራሮች ሥነምግባረዊ እንዲሆኑና ሙስናን እንዲከላከሉ በጋራ ለመስራት መኖሩን ገልፀዋል፡፡ ማዕከሉ ዓላማው በሀገር ደረጃ ጥሩ አመራርን ማፍራት ሥለሆነና የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ደግሞ ሥነምግባርን በመገንባት ሙስናን የሚከላከል በመሆኑ ለጋራ ውጤት በትብብር ማዕቀፍ እንደሚሰሩ አመላክተዋል፡፡

አመራር ከማልማት አንጻር ኃላፊነት ከተሰጠው ተቋምጋር አብሮ መስራት የሀብት ብክነትን ለመቀነስ ያስችላል ያሉት ኮሚሽነሩ፣ ችግር ፈቺ የአመራር ክፈተቶችን በማጥናት እና አመራሩን ለማብቃት የሚያስችል ሥልጠናዎችን በመስጠት አርዓያ ለሆኑት ደግሞ ዕውቅና እና ሽልማት በመስጠት በጋራ እንሰራለን ብለዋል፡፡

# ምንጩ ያልታወቀን ሀብት በመጠቀም በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ ከዘረፋ ከተመለሰው ሀብት እስከ 25% የሚሆነው ሀብት ለጠቋሚው ማበረታቻ ይሰጣል - ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ

የአብክመ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በክልሉ ውስጥ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የሀብት ምዝገባና የማሳወቅ እንዲሁም የማጣራት ስራ እያካሄደ ይገኛል፡፡



የአብክመ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሀብታሙ ሞገስ በዛሬው እለት ለአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን በሀብት ማሳወቅ፣ ምዝገባና ማረጋገጥ ዙሪያ መረጃ ሰጥተዋል፡፡ የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ እንዲሁም ማረጋገጥ ስራ ዓላማው የግልፀኝነትና ተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን፣ ተሿሚዎች፣ የህዝብ ተመራጮችና ለሙስና ተጋላጭ ከሆኑ መደቦች ላይ የተመደቡ/የተቀጠሩ ባለሙያዎች ስልጣናቸውን መከታ በማድረግ ከገቢ ምንጫቸው በላይ ሀብት ማካበት እንዳይችሉ እንዲሁም የጥቅም ግጭት እንዳይኖር ለመከላከል ታስቦ የተደረገ ነው ብለዋል ኮሚሽነሩ፡፡በመሆኑም ማንኛውም ሀብት አስመዝጋቢ በተገደበና በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ሀብቱን ማስመዝገብ እንዳለበት በአዋጅ የተቀመጠ መሆኑን ጠቅሰው ማንኛውም ሰው የሌላን ሰው ሀብት ህጋዊ በሆነ መልኩ ማወቅ ከፈለገ የማንኛውንም ሰው የሀብት መረጃ የማግኘትና የማየት መብት አለው ብለዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ማንኛውም ሰው ምንጩ ያልታወቀ ሀብት መኖሩን አውቆ በማስረጃ አስደግፎ ጥቆማ የሰጠ

ወደ ገጽ አራት ዞሯል...

## የመሬት አያያዝ መረጃን በማዘመን በዘርፉ የሚታየውን ብልሹ አሠራር ለመቅረፍ ከመቸውም ጊዜ በላይ ጠንካራ ሥራ መሥራት ይገባል - ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ



የመሬት አያያዝ መረጃን በማዘመን በዘርፉ የሚታየውን ብልሹ አሠራር ለመቅረፍ ከመቸውም ጊዜ በላይ ጠንካራ ሥራ መሥራት እንደሚገባ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማ መሠረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ ጠቁመዋል፡፡

ይህ የተጠቆመው በምክር ቤቱ 12ኛ መደበኛ ስብሰባ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት ሪፖርት በቀረበበት ወቅት ነው፡፡ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሚንስትር ክብርት ጫልቱ ሳኒ የተቋሙን የግማሽ ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት አቅርበው በምክር ቤቱ አስገምግመዋል፡፡

የአፈፃፀም ሪፖርቱ ከተደመጠ በኋላ የመሬት አያያዝ መረጃን በማዘመን በዘርፉ የሚታየውን ብልሹ አሠራር ለመቅረፍ



ከመቸውም ጊዜ በላይ ጠንካራ ሥራ መሥራት እንደሚገባ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ሸዊት ሻንካ አሳስበዋል፡፡ የምክር ቤት አባላት የመረጣቸውን ሕዝብ በሚያወያዩበት ጊዜ ሕዝቡ ቅሬታ ከሚነሳባቸው አንዱ የመንገድ ፕሮጀክቶች በመሆናቸው ሚንስቴር መ/ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ እንደሚገባ የተከበሩ ወይዘሮ ሸዊት ጨምረው አሳስበዋል፡፡

የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ችግሮች፣ እንዲሰሩ እቅድ ተይዞላቸው ያልተሰሩ መንገዶችን፣ ሥራቸው ተጀምሮ የተጓተቱ የመንገድ ፕረጀክቶችን፣ በከተሞች ያለው የመሬት አስተዳደር



ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጥ መሆኑንና በትክክል ካሳ ለተገመተላቸው የመሬት ባለቤቶች በወቅቱ ካሳ እየተከፈለ አለመሆኑን አንስተው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ምላሽና ማብራሪያ እንዲሰጣቸው የምክር ቤት አባላት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ክብርት ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ በሰጡት ምላሽ ማብራሪያ፤ ለክልልና ለፌዴራል ፕሮጀክቶች የሚሰጠው የካሳ ግምት የተለያየ በመሆኑ የምክር ቤት አባላት ሊረዷቸው እንደሚገባ ጠቁመው፤ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ችግር ያለበት



መሆኑን በጥናት ስላረጋገጡ በቀጣይ ትኩረት ሰጥተው የሚሠሩ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን አስመለክቶም ለተነሱ ጥያቄዎች በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ የሚሠሩ ተለይተው እንቅስቃሴ የተጀመረ በመሆኑ ችግሩ በየደረጃው የሚፈታ መሆኑን ጠቁመው፤ የመሬት መረጃ አስተዳደርን ለማዘመን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ለምክር ቤት አባላት አስረድተዋል፡፡

## የኮሚሽኑ አመራርና ሠራተኞች "ከዕዳ ወደ ምንዳ" በሚል ርዕስ ጉዳይ ላይ ውይይት አካሄዱ፡፡

የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ሀገርን ወደ ላቀ የእድገት ደረጃ ለማሻገር በሚያስችሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ከአመራሮች እና ሰራተኞች ጋር ውይይት አካሄዱ፡፡

"ከዕዳ ወደ ምንዳ" በሚል ርዕስ እንደ ሀገር እየተደረገ ያለዉን ውይይት ዓላማው የመንግሥት ሰራተኛውን ከእዳ ወደ ምንዳ ለመሸጋገር የሚያስችሉ ወቅታዊ፣ ሀገራዊ፣ ህዝባዊ እና መንግስታዊ አጀንዳዎች ላይ በመወያየትና በመመካከር የተሻለ ግንዛቤ በመፍጠር ሁሉም ዜጋ የበኩሉን ሚና እንዲወጣ ማስቻልና የሀገራችንን አንድነት ለማስቀጠልና ህዝባችንን ወደ ላቀ የእድገት ደረጃ ለማሻገር ያለመ ነዉ ተብሏል፡፡

በውይይቱ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር ክቡር አቶ እሸቴ አስፋዉ እንደገለፁት የስልጠናው ዓላማ





የመንግሥት ሰራተኛዉ የመንግሥት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን አዉቆ ስራውን እንዲሰራ ለማስቻል ነው ብለዋል፡፡ ኢትዮጵያ ሰፊ ታሪክ ያላት



ሀገር ናት ያሉት ኮሚሽነሩ ሰላምን በማምጣት፣ በቂ ሀብትን በመፍጠርና ያለዉን ሀብት በወጉ በማስተዳደር ወደፊት መራመድ ይገባል ብለዋል፡፡

ኮሚሽነሩ አክለውም ውይይቱ መልካም ነገሮችን ወደፊት በማምጣት የጋራ የሆነች ኢትዮጵያን መገንባት የሚያስችል ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡

በመድረኩ ሰነድ ቀርቦ ውይይት የተደረገ ሲሆን ከሰራተኞች እና አመራሮች ጥያቄዎችና ሀሳቦች ተነስተው ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡በውይይት መድረኩ ተገኝተው ለተነሱ ጥያቄችና ሀሳቦች ምላሽና ማብራሪያ የሰጡት የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) እንደ ሀገር ያለንን ሀብት አውቀን ሰላምን በጋራ በማስፈን በቁጭት መስራት አለብን ብለዋል፡፡

ኮሚሽነሩ አክለውም የልማት ሥራዎችን ሲሰሩ ተግዳሮቶች ቢኖሩም ተግዳሮቶችን ወደ እድል እየቀየርን መስራት አለብን፥ ይህንን ማድረግ ደግሞ የሁሉም ሀላፊነት ነው ብለዋል፡፡

ወደ ገጽ 5 ዞሯል...

## በፍርድ ቤት ያላቸውን ክርክር ለማሸነፍ ለዳኛ ጉቦ ሊሰጡ የነበሩ ወንድማማቾች በእስራት ተቀጡ



በኢሉባቡር ዞን ሱፔ ሶዶ ወረዳ ውስጥ በፍርድ ቤት ያላቸውን ክርክር ለማሸነፍ ጉዳያቸውን ለያዘችው ዳኛ ጉቦ ሊሰጡ የነበሩ ሁለት ወንድማማቾች ዳኛዋ በሰጡት ጥቆማ መሰረት በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የኢሉባቡር ዞን ፖሊስ መምሪያ ገልጿል:: የኢሉባቡር ዞን ፖሊስ መምሪያ የኮሙኒኬሽን ፅ/ቤት ኃላፊ ምክትል ኢንስፔክተር ለማ ቦይዶ እንደገለፁት አንደኛ ተከሳሽ ተመስገን ባቡና ሁለተኛ ተከሳሽ ፌደስ ባቡ የተባሉ ሁለት ወንድማማቾች ድርጊቱን ፈፅመዋል::

ወንድማማቾቹ በፍርድ ቤት ያላቸውን ክርክር በገንዘብ ለማሸነፍ እና የፍትህ ሂደቱን ለማስቀየር ጉዳያቸውን ለያዘችው ዳኛ 2,500 ብር ለመስጠት ሲዘጋጁ ዳኛዋ ለፖሊስ በሰጡት ጥቆማ መሰረት ሁለቱም እጅ ከፍንጅ በቁጥጥር ስር ውለዋል:: የምርመራ መዝገባቸውም በፖሊስ ተጣርቶ መዝገባቸው ለዓቃቤ ህግ ተልኳል::

ዓቃቤ ህግም የምርመራ መዝገቡን ተመልክቶ ለኢሉባቡር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ይመሰርታል:: ክሱን የተመለከተው የኢሉባቡር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለቱ ወንድማማቾች ጥፋተኛ መሆናቸውን አምኖ እያንዳንዳቸው በ1 ዓመት ከ 6 ወር ቀላል እስራት እና በ2,000 ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ መወሰኑን ኢንስፔክተር ለማ ቦይዶ ጨምረው ተናግረዋል::

ከገጽ ሁለት የዞረ...

እና የተጠቀመው ሀብት መኖሩ ተረጋግጦ በፍትህ ክስ ተመስርቶበት በፍ/ቤት ጥፋተኛነቱ ታውቆ ለመንግስት የሚመለስ ሀብት ካለ ለጠቋሚው ከሚመለሰው ሀብት እስከ 25% የሚደርስ ሀብት ጠቋሚው የማግኘት መብት አለው ብለዋል:: ኮሚሽኑ አክለውም በዚህ ዓመት ሙስናን ለመከላከል ያጋጠሙ ችግሮች ወቅታዊ የክልሉ የሰላም አለመረጋጋትና ሁሉም ተቋማት በሚፈለገው ልክ አገልግሎት እየሰጡ ባለመሆኑ ምክንያት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር፣ ለዘረፋና የማጭበርበር ተግባር ለሌቦች አመች ሁኔታ ፈጥሯል፤ የፀጥታ አካላት በወቅታዊ ስራ በመጠመዳቸው ምክንያት የሙስና ወንጀል የፈፀሙ አካላትን ተከታትሎ መያዝ አለመቻል፣ ህብረተሰቡ በሚፈለገው ልክ ተዘዋዉሮ ጥቆማዋችንና ማስረጃዎችን ማድረስ አለመቻሉ በፀረ-ሙስና ትግሉ ላይ የመቀዛቀዝ ሁኔታ ፈጥሯል ብለዋል:: እንደኮሚሽን በተቋማት ውስጥ የህዝብን እሮሮ በመስማትና ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ ተቋማትን በመለየት የአሰራር ስርዓት ጥናት በማድረግ ብልሹ አሰራሮች እንዲስተካከሉ በማድረግ፤ በክልሉ ውስጥ ያሉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችንና አጋር አካላትን በማጠናከር ወደ ሙስና መከላከል ተግባር እንዲገቡ እየተደረገ መሆኑን ገልፀው፤ ሙስናን በዚህ ተቋም ብቻ መከላከል ስለማይቻል ሁሉም የህብረተሰብ ክፍልና ተቋማት ድጋፍና ተሳትፎ ይጠይቃል ብለዋል:: የፀረ-ሙስና ትግሉን ይበልጥ ለማቀጣጠል ህብረተሰቡ በባለቤትነት ይዞ ጥቆማዎችንና ማስረጃዎችን በመስጠት እንዲሁም አጋር አካላት ከዚህ በፊቱ የተሻለ ቅንጅት በመፍጠር ሁሉም አካባቢ እየታዩ ያሉ የሙስና ወንጀሎችን በጋራ ለመከላከል ጥረትና ትግል ያስፈልጋል ብለዋል::

## የልማት ሥራ ውጤታማ እንዳይሆንና በገቢ አሰባሰብ ሂደት ላይ ማነቆ የሚፈጥሩ ከአመራሮች ጀምሮ እስከ ባለድርሻ አካላት ድረስ ብልሹ አሠራር ውስጥ ሲገቡ በሕግ ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል - የውይይቱ ተሳታፊዎች

የወላይታ ዞን መንግሥት ረዳት ተጠሪ አቶ ተመስገን ዓለማየሁ በንቅናቄው መድረኩ ላይ በከተማው የስራ አጥነት ችግር፣ የኑሮ ውድነት እና የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ለመመለስ የውስጥ ገቢ አሟጦ መሰብሰብና ህዝቡን ማሳተፍ ቁልፍ ነው ብለዋል:: የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ ያለመዘመኑና በሀሰተኛ ደረሰኞች ምክንያት መገኘት የሚገባው ገቢ እንዳይገኝ ማነቆ ሆኖ መቆየቱን ተናግረዋል::









የአረካ ከተማ ከንቲባ አቶ ደመቀ ደጀኔ በበኩላቸው በከተሞች ሁለንተናዊ ዕድገት ለማረጋገጥ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎቸን፣ ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶችን በመንደፍ ሰፌ ርብርብ በማድረግ መሬት ላይ ለማውረድ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል::

የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች በማዘመን እና ዲጂታላይዝ በማድረግ ለህብረተሰቡ የሚቀርብ አገልግሎት ተደራሽ፣ ፍታሃዊና ቀልጣፋ መሆን ይገባል ብለዋል:: በልማት ሥራ ላይ ሥር ነቀል ውጤት ለማምጣት በገቢ አሰባሰብ በየደረጃው ካለው አመራር ጀምሮ እስከ ኅብረተሰብ ክፍል ድረስ ብልሹ አሠራር ውስጥ ሲገቡ ተጠያቂ ሊሆን ይገባል ብለዋል አስተያየት ሰጪዎች:: በከተሞች አካባቢ የሚስተዋሉ ብልሹ አሠራርን በማስወገድና ተጠያቂነትን በማስፈን ቀጣይነት ያለው ልማት ለማምጣት በገቢ አሰባሰብ ላይ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ጠቁመዋል:: የአረካ ከተማ አስተዳደር ብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ አድማሱ አይዛ ኅብረተሰቡ ከመንግሥት ጋር ከተባበረና ከተጋገዘን የልማት ሥራን ማፋጠን ቀላል እንደሆነ ገልፀዋል::

የአገልግሎት አሰጣጡ የህዝቡን እርካታ ያረጋገጠ እና ከእጅ መንሻ፣ ጉቦና ምልጃ ነጻ በሆነ መልኩ ለሁሉም ነዋሪዎች በፍትሃዊነት የሚሰጥ መሆኑን ማረጋገጥ ወሳኝ ተግባር አድርጎ መዉሰድና በትኩረት እንደሚፈጸም ይሰራልም ነው ያሉት:: በከተሞች

ወደ ገጽ 6 ዞሯል...

# የዜጎችን የፍትህ ፍላጎት በማርካት በፍትህ ሥርዓቱ ላይ ያለውን ዕምነት ማሳደግ እንደሚገባ ተጠቆመ



የፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ክቡር ጌዲዮና ጢሞቲዎስ (ዶ/ር) ከምክር ቤቱ ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ዝርዝር ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የፍትህ ሥርዓቱን ዲጂታላይዝ ለማድረግና በቴክኖሎጂ ለማገዝ ምን ጥረት እየተደረገ ይገኛል፣ ለጠቋሚዎችና ለምስክሮች እየተሰጠ የሚገኝ የህግ ከለላ ምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ እና ሌሎችም ጥያቄዎች ከምክር ቤቱ አባላትና ከህግና ፍትህ ቋሚ ኮሚቴ ተነስተዋል፡፡

ከህዝብና ከመንግስት የተመዘበሩና ወደ ሌሎች አገራት የሸሹ ሀብቶችን ለማስመለስ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ምን ይመስላሉ፣ ባህላዊ የፍትሕ ሥርዓትን ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ምን ታስቧል፣ ለታራሚዎች የሚሰጥ ምህረት ለብልሹ አሰራር ተጋልጧል፣ በማረሚያ ቤቶች ውስጥ ያለው የመሰረታዊ አገልግሎት አቅርቦት ችግር አለባቸው የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለተነሱ ጥያቄዎች የፍትህ ሚንስትሩ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ዘርፉን በቴክኖሎጂ ከማዘመን አንፃር የሰነዶችን ምዝገባና ማረጋገጥ ፋይሎችን ማደራጀትን ክፍያዎችን የመፈፀም አገልግሎቶች መጀመራቸውን የገለፁት ሚንስትሩ፥ ፋይሎችን የፍትህ ሂደት መከታተያ ዘዴዎች በመበልፀግ ላይ ይገኛሉ ብለዋል፡፡ ወደ ውጪ አገራት የአገር ሃብትን ይዘው የሚኮበልሉ ተጠርጣሪዎችን በብዛት የሚኮበሉልባቸውን አገራት በመለየት ከሀገራቱ ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችል የማዕቀፍ ስምምነቶች እየተፈፀሙ ይገኛሉ ያሉ ሲሆን፥ የተባበሩት አረብ ኤሜሬትስና ደቡብ አፍሪካ እንደሚገኙበት ጠቁመዋል፡፡

የኦዲት ግኝት ያለባቸውን ተቋማት ተጠያቂ ለማድርግ በዘርፉ ዕውቅና እና ልምድ ያለው የሰው ሃይል ዕጥረት መኖሩን የጠቆሙት ሚኒስትሩ፥ ለምስክሮችና ለጠቋሚዎች ከሚሰጥ የህግ ከለላ አንጻር አገራችን የህግ ክፍተት ባይኖርባትም የሃብት ዕጥረት መኖሩ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም ብለዋል፡ ፡ የባህላዊ ፍትህ ሥርዓቱን ለመጠቀም ከየክልሎቹ ባህልና ዕሴት ጋር የተስማማ የፍትህ ሥርዓት ረቂቅ ሞዴል ተዘጋጅቶ ከክልሎች ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጠም ወደ ስራ ለመግባት በዝግጅት ላይ እንሚገኝ ለምክር ቤቱ አብራርተዋል፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት መንግስቱ በበኩላቸው የፍትህ ሚኒስቴር ሰዎችን በህገ ወጥ መንገድ በማዘዋወር ለእንግልት በሚዳርጉ ህገ ወጥ ደላሎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ለሌሎች አስተማሪ መሆን ይገባዋል ብለዋል፡፡ ለታራሚዎች ምህረት የሚሰጥባቸው ዕድሎችን አሰራሮችን ግልፅ ማድረግ እንደሚገባ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ አሳስበዋል፡፡የማህበረሰቡን የፍትህ ፍላጎት ለማርካትና በሥርዓቱ ላይ ያለውን ዕምነት ማሳደግ እንደሚገባ የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት የጠቆሙ ሲሆን፤ አቅም ለሌላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች የሚሰጠው ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎትም በስፋት ተደራሽ ሊደረግ እንደሚገባው ገልፀዋል፡፡





ከገጽ 4 የዞረ......

የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር አቶ ወዶ አጦ በበኩላቸው ኢትዮጵያ ብዙ ሀብት ያላትና ሀብቷን አውቀን በጋራ ከሰራን ለነገ ብዙ ተስፋ ያላት ሀገር ናት ብለዋል፡፡ እንደ እኛ ተቋም የሥነምግር ብልሹነትን በማረም እና ሙስናን በመከላከል ሀብት እንዳይመዘበር በጋራ መስራት አለብን ሲሉ አጽንኦት ሰጥተዋል፡፡

ውይይቱ በሁለት ምዕራፎችና በአራት ርዕሶች ተከፍሎ ተሰጥቷል፡፡

## ማንኛውንም ጉዳይ አስፈጽማለሁ በማለት ህብረተሰቡን በማጭበርበር ገንዘብ ሲቀበል የነበረ ግለሰብ በቁጥጥር ስር መዋሉ ተገለፀ



በወላይታ ሶዶ ከተማ በፋና ወምባ ቀበሌ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት የቤቶች ልማት ዘርፍ ባለሙያ አቶ ሄኖክ ቴጋ ማንኛውንም ጉዳይ አስፈጽማለሁ በማለት ህብረተሰቡን በማጭበርበር ገንዘብ ሲቀበል በቁጥጥር ሥር መዋሉን የከተማው ፖሊስ አስታወቀ:: በህግ ቁጥጥር ስር የዋለው ግለሰብ የማዘጋጃ ቤቱ ስራ አስኪያጅ ጓደኛዬ ነው፥ ጉዳያችሁን እኔ አስፈጽማለሁ በማለት ህብረተሰቡን ሲያጭበረብርና ገንዘብ ሲቀበል እንደነበረ ፖሊስ ገልጿል::ግለሰቡ በተለያዩ ጊዜያት ከባለጉዳዮች የቀበሌ ቤት እኔ እሰጣለሁ፣ የትኛውንም ሥራዎችን እኔ አስፈጽማለሁ፣ የማዘጋጃ ቤቱ ስራ አስኪያጅ ጓደኛዬ ነው በማለት ገንዘብ ሲቀበል እንደነበር የተገለፀ ሲሆን፥ ግለሰቡ የተለመደ የማጭበርበር ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ተይዟል::



የወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል በልዩ ትኩረት እየሰራ በመሆኑ ማንኛውም ባለጉዳይ አገልግሎት ለማግኘት ወደ ተቋማት ሲሄድ እጅ መንሻ፣ ጉቦ እና ያልተገባ ጥቅም የሚጠይቁ ግለሰቦች ሲያጋጥም ለህግ አካላት ጥቆማ እንዲሰጡ ጥሪ አቅርባል:: ስለሆነም በከተማው ፖሊስ የስልክ መስመር 04655510146 በመደወል ሙሰኞችንና መሰል ድርጊት ፈፃሚዎችን በማንኛውንም ሰዓት ጥቆማ እንዲሰጡ የወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር አሳስቧል::

## ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በማዘጋጀት ወንጀል የተከሰሰው የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ሰራተኛ በእስራት ተቀጣ



ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃን በማዘጋጀት ወንጀል የተከሰሰው የሻንቡ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ሰራተኛ በ8 ዓመት ከ5 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት ውሳኔ አሳለፈ:: የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ የሙስና ጉዳዮች ዐቃቤ ሕግ የሙስና አዋጅ 881/2007 ድንጋጌን መተላለፉን ጠቅሶ ሶሬሳ አፋታ ላይ ክስ መስርቶበታል::

ተከሳሹ በጥር 17 ቀን 2015 ዓ.ም በሻንቡ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ውስጥ የተማሪዎች ምዝገባ ኦፊሰር ሆኖ ሲሰራ በተቋሙ አመራሮች ፊርማ የተዘጋጀ የሚመስል ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎችና የሙያ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቶችን በ34 ግለሰቦች ስም አዘጋጅቶ የተገኘ መሆኑ በክሱ ዝርዝር ላይ ተጠቅሷል::

በዚህ መልኩ የቀረበበት ክስ ለተከሳሹ እንዲደርስ ከተደረገ በኋላ ተከሳሹ ወንጀሉን አለመፈጸሙን ጠቅሶ የዕምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቷል:: ይህን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን የሰውና የሰነድ ማስረጃን መርምሮ በተከሰሰበት ድንጋጌ እንዲከላከል ብይን የሰጠ ቢሆንም ተከሳሹ መከላከል ባለመቻሉ የጥፋተኝነት ፍርድ ተላልፎበታል:: ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኝ የቅጣት አስተያየትን ከመረመረ በኋላ ተከሳሹን ጥፋተኛ በተባለበት ድንጋጌ በ8 ዓመት ከ5 ወራት ጽኑ እስራትና በ1 ሺህ ብር ገንዘብ እንዲቀጣ ወስኗል::

## በመዲናዋ በሙስና መከላከል ሥራ ከ876 ነጥብ 9 ሚሊየን ብር በላይ ማዳን መቻሉ ተገለጸ



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር አቶ አሰፋ ቶላ እንዳሉት፥ ባለፉት ስድስት ወራት ሙስናን ለመከላከል የሚያስችሉ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና ሌሎች ሥራዎች ተከናውነዋል:: ከዚህ ባለፈም ሙስና በስፋት የሚስተዋልባቸው ዘርፎችን በመለየት የመከላከል ሥራ ላይ በትኩረት መሰራቱን ነው የገለጹት::

በዚህም በመደበኛ ሙስና መከላከል 534 ነጥብ 5 ሚሊየን ብር እና በአስቸኳይ ሙስና መከላከል 342 ነጥብ 4 ሚሊየን በድምሩ 876 ነጥብ 9 ሚሊየን ብር በላይ ሃብት ማዳን መቻሉን አንስተዋል::

በተጨማሪም በአይነት 171 ጠቅላላ ንብረት እና ከ4 ሺህ 685 ካሬ ሜትር በላይ መሬት ማዳን መቻሉን አስረድተዋል:: ከሙስና ወንጀሉ ጋር በተያያዘም 136 ሰዎች ተጠያቂ መደረጋቸውን ምክትል ኮሚሽነሩ ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ተናግረዋ:: በተጠቀሰው ጊዜ 792 ጥቆማ መቅረቡን ጠቁመው፥ ከእነዚህ ውስጥ የተጠና 592 እና አግባብነት የሌላቸው 21 ሲሆን፥ ቀሪዎቹ ደግሞ በሒደት ላይ እንደሚገኙ ጠቅሰዋል::

ከገጽ 3 የዞረ......

ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ እና ተወዳደሪ ከተሞችን ለማድረግ የዉስጥ አቅም ማጎልበት የሞት ሽረት ትግል የሚጠይቅ አጀንዳ ነው ብለዋል:: የከተማው ነዋሪዎች እና ሁሉም ባለድርሻ አካላት በገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዙሪያ የሚስተዋል በተለያዩ አካላት የሚገለጽ ኪራይ ሰብሳቢነትን ለማስቀረት የሚካሄድ ብርቱ ትግል መደገፍና ዉጤታማ እንዲሆን የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበትም ተገልጿል:: የልማት ሥራ ውጤታማ እንዳይሆንና በገቢ አሰባሰብ ሂደት ማነቆ የሚሆኑ አመራሮች ጀምሮ እስከ ኅብረተሰብ ክፍሉ ድረስ ብልሹ አሠራር ውስጥ ሲገቡ በሕግ ተጠያቂ ሊሆን ይገባል ብለዋል የወይይቱ ተሳታፊዎች:: መንግስት የልማት ሥራ እንዳይሰራ የሰለጠኑና ለሕዝብ ልማት ቦታ የማይሰጡ አጨበርባሪ አካላት በሕግ መጠየቅ ተገቢ መሆኑን የውይይቱ ተሳታፊዎች ጠቁመዋል:: በመድረኩ የከተማ አመራሩ፣ ከተማ ነዋሪ የተወጣጡ ህብረተሰብ ክፍሎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል::

## በሥነምግባር የታነፀና የህብረተሰብ ጥቅም የሚያከብር ትውልድ ለመፍጠር ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ተጠየቀ

የአዲስ አበባ ከተማ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን "በትውልድ ሥነምግባር ግንባታ እና ፀረ-ሙስና ጉዳዮች" ትኩረት አድርገው በተዘጋጁ የስልጠና ሞጁሎች ላይ ማረጋገጫ አውደ ጥናት አካሄደ፡፡





በአውደ ጥናቱ ላይ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ጀማል ረዲ እንደገለፁት ለሀገር ዕድገትና ለልማት ፀር የሆነውን ሙስናን ለመዋጋት የዜጎችን ሥነምግባር መገንባት ይገባል ብለዋል፡፡ አክለውም በሥነምግባር የታነፀና የህብረተሰቡን ጥቅም የሚያከብር ትውልድ ለመፍጠር ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር አሰፋ ቶላ በበኩላቸው የአውደ ጥናቱ ዓላማ የትውልድ ሥነምግባር ግንባታና ሙስናን በመለየት ለመከላከልና ለመፍታት የሚያስችል ዕውቀትና ክህሎት ለማስታጠቅ የተዘጋጀውን የስልጠና ሞጁሎች ለማረጋገጥ ነው ብለዋል፡፡ የፀረ-ሙስና ትግል የግለሰብ ብቻ ሳይሆን የጋራ ኃላፊነት ጭምር መሆኑን የጠቆሙት ምክትል ኮሚሽነሩ፣ በዚህ አውደ ጥናት ለራሳችን እና ለመጪው ትውልድ የተሻለ ሁኔታ ለመገንባት ያለንን ቁርጠኝነት ለማሳየትና የስልጠና ሞጁሎቹን ለማዳበር በቂ አስተያየት መስጠት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ በአውደ ጥናቱ ላይ በሥነምግባርና መልካም አስተዳደር፣ የሙስና ጽንሰ ሀሳብ እና የመከላከል ስልቶች፣ የሃብት ማሳወቅ እና ማስመዝገብ ስርዓት፣ ሙስናና የመንግስት ግዢ፣ የሙስና ወንጀል ምርመራ፣ የጥቅም ግጭት መከላከልና ማስተዳደር፣ የሙስና ወንጀል በጠቅላላው፣ የፖሊስና ዓቃቢ ህግ የሙያ ሥነምግባር፣ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት እና ሥነምግባራዊ አመራር በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በዝርዝር ቀርበው በተሳታፊዎች ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡

## የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ማዕከል ከተሞችን የመሬት መረጃ አያያዝ ስርዓት የማዘመኑ ተግባር ተጠናክሮ መቀጠሉ ተገለጸ

የከተሞች የመሬት መረጃ አያያዝ ስርዓት ማዘመን መሬት ለህገ-ወጥ ተግባር ተጋላጭ እንዳይሆንና ነዋሪዎች ላፈሩት ሀብት ዘላቂ ዋስትና እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ተመልክቷል፡፡





ክልል አቀፍ የከተሞች ንቅናቄ መድረክ በአርባ ምንጭ ከተማ በተካሄደበት ውቅት የተገኙት የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ እንዳሉት፤ በክልሉ ከተሞች የመሬት መረጃ አያያዝ ስርዓት ባለመዘመኑ ለህገ-ወጥ ተግባራት ሲጋለጥ ቆይቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የክልሉ መንግስት የከተሞችን ልማት በማፋጠን የህዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እያደረገ ያለውን ጥረት እያደናቀፈ ይገኛል ብለዋል፡፡ የመሬት አስተዳደር ስርዓትን ለማዘመን ቀደም ሲል ጥረት ቢደረግም የሚፈለገው ለውጥ ማምጣት አለመቻሉን ጠቅሰው፤ የከተማ መሬት በአግባቡ በመለየትና በመመዝገብ ችግሩን ማቃለል እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡ ለዚህም እስከ መጪው ሰኔ 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ የክልሉ ማዕከል የሆኑት ሶዶ፣ አርባ ምንጭ፣ ዲላ፣ ጂንካ፣ ሳውላና ካራት ከተሞች የሚገኝ ማንኛውም የመሬት መረጃ ስርዓት ማዘመን የሚያስችል መመሪያ በማዘጋጀት ወደ ተግባር ለመግባት የክልሉ መንግስት እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

የክልሉ ማዕከል ከተሞችን የመሬት መረጃ አያያዝ ስርዓት የማዘመኑን ስራ አጠናክሮ ለማስቀጠል እየተካሄደ ያለውን ስራ ለማሳካት የዘርፉ አመራሮችና ባለሙያዎች ሃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ ከተሞችን የብልጽግና ማዕከል ለማድረግ የክልሉ መንግስት በትኩረት እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ የአመራር አባላት በውጤት የታጀበ ስራ በማከናወን የታሪክ ተወዳሽ ለመሆን በቁጠኝነት መምራት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል፡፡ በክልሉ ጎፋ ዞን የሳውላ ከተማ ከንቲባ አቶ ታምራት ተሰማ በበኩላቸው፤ እስካሁን የነበረው የከተማ መሬት መረጃ አያያዝ ስርዓት ችግሮችን በዘላቂነት የሚፈታ ሆኖ ባለመገኘቱ ህገ-ወጥነት እየተስፋፋ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

በከተማ አስተዳደሩ በሊዝ የተላለፉና ነባር ይዞታዎች እንዲሁም በማስፋፊያ አካባቢዎች የሚገኙ የመሬት ምዝገባ ስርዓት ውስጥ ለማስገባት እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ እስከ ሰኔ 30 ለዲጅታል መረጃ ስርዓት መሠረት የሚሆን የማኑዋል መረጃ ስራ እናጠናቅቃለን ብለዋል፡፡ የአመራር አባላት ቁርጠኛ ያለመሆንና ደላሎች በሚፈጥሯቸው ችግሮች ምክንያት አጠቃላይ የመሬት አስተዳደር ስርዓቱ ማዘመን አለመቻሉን የገለጹት ደግሞ የወላይታ ሶዶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ፋንታሁን ዮናስ ናቸው፡፡ በነበረው የሶዶ ከተማ መሬት መረጃ በካዳስተር 10 በመቶ ብቻ መያዝ መቻሉን ጠቅሰው፤ የክልሉ መንግስት በያዘው አቋም ልክ የከተማ የመሬት መረጃ አያያዝ ስርዓት ለማዘመን ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ እስከ ሰኔ 30 ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ የበኩላቸውን እንደሚወጡ አስታውቀዋል፡፡ የመሬት መረጃ አያያዝ ስርዓት ማዘመን መሬት ለህገ-ወጥ ተግባር ተጋላጭ እንዳይሆን የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ ነዋሪዎች ላፈሩት ሀብት ዘላቂ ዋስትና የሚሰጥና የገቢ አሰባሰብን በማሻሻል የከተሞችን ዕድገት ለማፋጠን ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ተመልክቷል፡፡

## በሙስና ወንጀል የተከሰሱት የቀድሞ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት የመረጃ ክትትልና ትንተና ቡድን መሪ አቤል ጌታቸው በጽኑ እስራትና በገንዘብ ተቀጡ



የቀድሞ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት የመረጃ ክትትል እና ትንተና ቡድን መሪ አቤል ጌታቸው እና በግል ሥራ የሚተዳደሩት አቶ ፉፋ ዳባ ጥፋተኛ በተባሉበት ድንጋጌ በእስራትና በገንዘብ እንዲቀጡ ተወሰነ:: የቅጣት ውሳኔውን ያስተላለፈው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው:: የፍትሕ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በተከሳሾቹ ላይ ሁለት ክሶችን አቅርቦ ነበር::

አቤል ጌታቸው በተባለው ግለሰብ ላይ የቀረበው ክስ ተከሳሹ የሙስና ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9 ንዑስ ቁጥር 1 እና ንዑስ ቁጥር 2 ስር የተጠቀሰውን ድንጋጌ ተላልፏል የሚል ነው:: ሁለተኛ ተከሳሽን ፉፋ ዳባን በሚመለከት ደግሞ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረትን ሕጋዊ አድርጎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 780/2005 አንቀጽ 29 ንዑስ ቁጥር 1 ሀ፣ ስር ያለውን ድንጋጌ በመተላለፍ የሚል ክስ ነው የቀረበው:: አቶ አቤል ጌታቸው የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ውስጥ የመረጃ ክትትልና ትንተና ቡድን መሪ ሆነው ሲሰሩ የተቋሙን አሰራር ባልተከተለ መልኩ የባለሃብቶችንና የድርጅቶችን የባንክ ሒሳብ አስቀድሞ በማጥናትና መረጃ በመውሰድ በተለያዩ ጊዜያት ለባለሃብቶች ስልክ በመደወል በአካል በማግኘት ገንዘብ እንዲከፍሉ በመጠየቅ የማይከፍሉ ከሆነ ደግሞ የፋይናንስ እንቅስቃሴያቸውን በተመለከተ ለፖሊስ በማስተላለፍ የወንጀል ክስ እንደሚመሰረትባቸው በመግለጽ አስፈራርተዋል በማለት ነው ዐቃቤ ሕግ በክሱ የጠቀሰው:: በዚህ መልኩ ተከሳሹ በ2013 እና በ2014 ዓ.ም በተለያዩ ጊዜያት ባለሃብቶችን በማስፈራራት ከ3 ግለሰቦች 3 ሚሊየን 70 ሺህ ብር ገንዘብ ፉፋ ዳባ በተባለው 2ኛ ተከሳሽ ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገንዘቡ ገቢ እንዲደረግ በማድረግ በዋና ወንጀል አድራጊነት ስልጣንን ያለአግባብ መገልገል ከባድ ሙስና ወንጀል ክስ ቀርቦበት ነበር::


ሁለተኛ ተከሳሽ ፉፋ ዳባን በሚመለከት ደግሞ በወንጀል የተገኘ 3 ሚሊየን 70 ሺህ ብር የወንጀል ፍሬ መሆኑን እያወቁ የገንዘቡን ምንጭ ለመደበቅ በስሙ በባንክ የገባውን ገንዘብ በተለያዩ መጠን በመጠቀም ሕገ ወጥ ገንዘብን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ የሚል ክስ በዐቃቤ ሕግ ቀርቦበታል:: በዚህ መልኩ ክሱ ለተከሳሾች የክስ ዝርዝሩ ደርሷቸው በችሎት በንባብ ተሰምቷል:: ከዚህም በኋላ ተከሳሾች የሰጡትን የዕምነት ክህደት ቃል ተከትሎ ፍርድ ቤቱ በዐቃቤ ሕግ የቀረቡ አምስት የሰው ምስክሮችን ቃል እና የሰነድ ማስረጃ መርምሮ ተከሳሾቹ እያንዳንዳቸው በተከሰሱበት ድንጋጌ እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል:: ይሁንና ተከሳሾቹ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን በተገቢው መከላከል አለመቻላቸውን ጠቅሶ ፍርድ ቤቱ የጥፋተኝነት ፍርድ አስተላልፎባቸዋል::

ፍርድ ቤቱ ከዚህም በኋላ የግራ ቀኝ የቀረቡ የቅጣት ማክበጃና የቅጣት ማቅለያ አስተያየቶችን መርምሯል:: በዚህም አንደኛ ተከሳሽ አቶ አቤልን በሚመለከት በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ በሰላም ማስከበር ረገድ እንዲሁም በበጎ አድራጎት ድርጅት ውስጥ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ጨምሮ አጠቃላይ ያቀረበውን የቅጣት ማቅለያ አስተያየቶችን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 86 እና በአንቀጽ 82 ንዑስ ቁጥር 1 (ሀ) መሰረት አጠቃላይ 7 የቅጣት ማቅለያ አስተያየቶችን ፍርድ ቤቱ ይዞላቸዋል:: ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ የቅጣት ማክበጃ አስተያየት ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በዝቅተኛ ደረጃ በመያዝ አንደኛ ተከሳሽን በዕርከን 16 መሰረት በ3 ዓመት ጽኑ እስራትና በ1 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ፍርድ ቤቱ ወስኗል:: ሁለተኛ ተከሳሽ ፉፋ ዳባ ደግሞ በዕርከን 22 መሰረት በ5 ዓመት ከ 6 ወራት ጽኑ እስራት እና በ6 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል:: ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ ይግባኝ እንደሚጠይቅ ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ገልጿል::

## የኮሚሽኑ አመራሮች እና ሠራተኞች የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያዘጋጀውን የዲፕሎማሲ አውደ ርዕይ ጎበኙ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራሮች እና ሠራተኞች የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያዘጋጀውን የዲፕሎማሲ አውደ ርዕይ ጎብኝተዋል::

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር "የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ሳምንት" በሚል መሪ ቃል በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀዉን የሀገራችንን የዲፕሎማሲ ታሪክ፣ ወቅታዊ የዲፕሎማሲ ክንውኖች እና የመጪውን ዘመን ርዕይ እንዲሁም በመስኩ ሀገራችን



ለዓለም ያበረከተችውን አስተዋፅኦ ለዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ እና ለህዝብ ለማስተዋወቅ ባዘጋጀው የዲፕሎማሲ አውደ ርዕይ ላይ የኮሚሽኑ አመራሮች እና ሠራተኞች ጉብኝት አድርገዋል::



## ኮሚሽኑ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ እንዲሁም ማጣራት ስራ እያካሄደ እንደሚገኝ ገለፀ



የአብክመ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ዳ/ዳይሬክተር አቶ ይልቃል ወርቅነህ በሀብት ማሳወቅና ምዝገባ እንዲሁም ማጣራት ላይ ለጋዜጠኞች መረጃ ሰጥተዋል:: አቶ ይልቃል በመግለጫቸው የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ዋና ዓላማው የግልፀኝነትና ተጠያቂነት ስርዓት ለማስፈንና ተሿሚዎች ስልጣናቸውን ያለአግባብ መከታ አድርገው ከገቢ ምንጫቸው በላይ ሀብት ማካበት እንዳይችሉ እንዲሁም የጥቅም ግጭት ለመከላከል መሰረት ያደረገ ነው ብለዋል::

ሀብት ማስመዝገብ ያለባቸው አካላት የህዝብ ተመራጮች፣ በየትኛውም እርከን ላይ ያሉ የመንግስት ተሿሚዎች እና ለሙስና ተጋላጭ ከሆኑ መደቦች ላይ የተመደቡ/የተቀጠሩ ባለሙያዎችን መሆናቸውን ገልፀዋል:: ሀብት አስመዝጋቢዎች የመጀመሪያ ምዝገባ ሀብታቸውን ማስመዝገብ ያለባቸው የህዝብ ተመራጮች በተመረጡ፣ የመንግስት ተሿሚዎች በተሾሙ እና ባለሙያዎች በተቀጠሩ ወይም በተመደቡ በ45 ቀናት ውስጥ ሲሆን፥ ለእድሳት ደግሞ የመጀመሪያ ምዝገባ ካስመዘገቡ በኂላ በ2.5 (በሁለት ዓመት ከአምስት ወር) መሆኑን በመግለጫው አንስተዋል::

አቶ ይልቃል አክለውም ሀብት አስመዝጋቢዎች በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት ሀብታቸውን ሳያስመዘግቡ ከቀሩ ለመጀመሪያ ጊዜ 1000 ብር ይቀጡና በ30 ቀናት ውስጥ ማስመዝገብ ይኖርባቸዋል ብለዋል:: በመደበኛም ሆነ በተራዘመላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሀብታቸውን ያላስመዘገቡ እና ትክክለኛ ሀብት ያላስመዘገቡ ካሉ እስከ 5 ዓመት የሚደርስ እስራት የሚያስቀጣና ማንኛውም ያልተመዘገበ ሀብት የሚወረስ መሆኑን በመግለጫቸው ገልፀዋል::

በመጨረሻም አቶ ይልቃል የሀብት ማሳወቅና ምዝገባ የሚካሄድባቸው ከወረዳ እስከ ክልል ባሉ ተቋማት በተመደቡ የሥነምግባር መኮንኖች፣ በደሴ፣ በጎንደርና ደብረ ብርሃን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በክልሉ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚካሄድ ሲሆን፥ ለሀብት ምዝገባው በየደረጃው የሚገኛው የተቋማት አመራሮች እገዛ ወሳኝ በመሆኑ በቅርበት ለሥነምግባር መኮንኖች የሀብት ምዝገባውን ሊያግዙና ሊያማክሩ ይገባል ብለዋል::

## የሥነ-ምግባር ጥሰት ፈጽመዋል በተባሉ አመራር እና ሰራተኞች ላይ እርምጃ መውሰዱን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት
Ethiopian Electric Utility

አገልግሎቱ በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ውስጥ የተጠያቂነት ስርዓትን ለማስፈን ባከናወነው ስራ እርምጃው መወሰዱን ነው የገለጸው:: ተቋሙ በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ውስጥ ከደንበኞች ከቀረቡለት 63 ጥቆማዎች ውስጥ የማጣርት ስራ በማከናወን፤ በ23 አመራር እና ሰራተኞች ላይ ላይ ከጹሑፍ ማስጠንቂያ እስከ ስንብት የሚደርስ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን መውሰዱን አስታውቋል:: በተጨማሪም በተቋሙ በውስጥ የሥነምግባር ችግር በታየባቸው 409 ሰራተኞች ላይ የተለያዩ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደወሰደም ገልጿል::

በዚህም በ106 ሰራተኞች ላይ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ በ282 ሰራተኞች ላይ የደመወዝ ቅጣት፣ በ11 ሰራተኞች ላይ ስንብት እንዲሁም በ10 ሰራተኞች ላይ ባደረገው ማጣራት ነጻ እንዳላቸው ከአገልግሎቱ የተገኘው መረጃ ያመላክታል:: ተቋሙ ከአገልግሎት አሰጣጡ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች እና ጥቆማዎችን ለመቀበል ከተዘረጉ የ905 እና 904 ነጻ የጥሪ ማዕከላት በተጨማሪ፤ ደንበኞች ቅሬታቸውን ቀላልና ምቹ በሆነ መንገድ ማቅረብ የሚችሉበት ዘመናዊ የሙስና ጥቆማ መቀበያ ስርዓት ለመዘርጋት በሂደት ላይ መሆኑን ተጠቁሟል::

# በሀሰተኛ ሰነዶች ግለሰቦች ሳያውቁ ቤታቸውን ለመሸጥ ከ15 ሚሊየን ብር በላይ የተቀበለው ተከሳሽ በእስራትና በገንዘብ ተቀጣ



የተለያዩ ሀሰተኛ ሰነዶችን በመጠቀም ግለሰቦች ሳያውቁ ቤታቸውን ለመሸጥ ከ15 ሚሊየን ብር በላይ ተቀብሏል የተባለው ተከሳሽ በጽኑ እስራትና በገንዘብ እንዲቀጣ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ወንጀል ችሎት ወሰነ፡፡ በአ/አ ከተማ ኮልፌ ቀራንዮ ፎሪና በግል ስራ የሚተዳደረው ተካ ዲኖ ሰይድ የሙስና አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 ንዑስ ቁጥር 2(ሀ) እና ንዑስ ቁጥር 3 ስር የተመላከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በተዘጋጁ ሀሰተኛ መንግስታዊ ሰነዶች መገልገል የሙስና ወንጀል እና በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል በፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ ክስ ቀርቦበት ነበር፡፡

ከቀረቡበት ክሶች መካከል ተከሳሹ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት፣ ለሌሎችም ለማስገኘት በማሰብ በመጋቢት ወር 2014 ዓ.ም ከስንታየው አበበ አወቀ ያልተሰጠውን ሀሰተኛ የውክልና ሰነድ፣ ሃሰተኛ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና ሃሰተኛ ያላገባ የምስክር ወረቀት በመጠቀም በፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ጽ/ቤት አቅርቦ ሽያጭ ውል መፈጸሙ ተመላክቷል፡፡

በፈጸመው የሽያጭ ውል መሰረት ደግሞ በስንታየው አበበ ስም ተመዝግቦ በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የሚገኘውን የቦታው ስፋት 94 ነጥብ 64 ካ/ሜትር የሆነ ጅምር የመኖሪያ ቤት ለግል ተበዳይ እንዳለ መኩሪያ ለመሸጥ በመስማማት በቅድሚያ 5 ሚሊየን 100 ሺህ ብር በባንክ ሂሳቡ እንዲገባለት በማድረግ እና የገባለትንም ገንዘብ ወደ ተለያዩ ግለሰቦች ሂሳብ በማስተላለፍ በሃሰት በተዘጋጁ መንግስታዊ ሰነዶች መገልገል የሙስና ወንጀል ተከሷል፡፡

በሁለተኛው ክስ ደግሞ ተከሳሹ ንብረትነቱ የአሊ ሃይረዲን መሃመድ የሆነ በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር አዲስ የሚገኘውን የመኖሪያ ቤት ለመሸጥ እንዲያስችለው በሃሰተኛ የተለያዩ ሰነዶችን በመጠቀም ከባለንብረቱ ያልተሰጠውን ውክልና እንደተሰጠው በማስመሰል ከመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት ያልተሰጠ ተመሳስሎ የተዘጋጀ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ኮፒ እና ከኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ወረዳ 05 ወሳኝ ኩነት የተሰጠ የሚል ሃሰተኛ የባለንብረቱ ያላገባ የምስክር ወረቀት ቅጂ በማቅረብ ቤቱን በ40 ሚሊየን ብር ለግል ተበዳይ እድሪስ ቡንሱር አብደላ ለመሸጥ መስማማቱ በክሱ ተጠቅሷል፡፡ በግንቦት 9 ቀን 2014 ዓ.ም ደግሞ የመንደር ሽያጭ ውል የተፈረመ ቅድሚያ ክፍያ 10 ሚሊዮን 500 ሺህ ብር ከግል ተበዳይ እድሪስ ቡንሱር የኦሮሚያ ህብረት ስራ ባንክ ቤተል ቅርንጫፍ ወደ ተከሳሽ የባንክ ሂሳብ ዝውውር የተፈጸመለት መሆኑም በክሱ ተጠቅሷል፡፡

> ሃሰተኛ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና ሃሰተኛ ያላገባ የምስክር ወረቀት በመጠቀም በፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ጽ/ቤት አቅርቦ ሽያጭ ውል መፈጸሙ ተመላክቷል፡፡

በአጠቃላይ ተከሳሽ ከአሊ ሃይረዲን ያልተሰጠውን ውክልና ሰነድ፣ ሃሰተኛ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና ሃሰተኛ ያላገባ የምስክር ወረቀት በማቅረብና የሽያጭ ውል በመፈጸም 10 ሚሊየን 500 ሺህ ብር በባንክ ሂሳቡ እንዲገባለት በማድረግና ገንዘቡን ወደተለያዩ ግለሰቦች ሂሳብ በማስተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሱ እና ለሌሎችም ያስገኘ በመሆኑ በፈጸመው በሃሰት በተዘጋጁ መንግስታዊ ሰነዶች መገልገል የሙስና ወንጀል ተከሷል፡፡

ከ4ኛ እስከ 5ኛ ባሉ ክሶች ላይ ደግሞ በተለያዩ ጊዜያት ከተለያዩ ግለሰቦች በባንክ ሂሳቡ የገባለትን ከ15 ሚሊየን ብር በላይ ለመደበቅ እና ከህግ ተጠያቂነት ለማምለጥ በማሰብ ገንዘቡን በተለያዩ ግለሰቦች ስም በተለያዩ መጠኖች በማስተላለፍ እንዲሁም በራሱ ስም ደግሞ በባንክ በተከፈተ ሂሳቡ ከ1 ሚሊየን ብር በላይ ያስተላለፈ መሆኑ ተጠቅሶ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ በማቅረብ ወንጀል ተከሶ ነበር፡፡

ተከሳሹ በዚህ መልኩ የቀረቡበት የወንጀል ድርጊት አለመፈጸሙን ጠቅሶ የሰጠውን የዕምነት ክህደት ቃል ተከትሎ ዐቃቤ ሕግ የሰውና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን የመረመረው ችሎቱ ተከሳሹ እንዲከላከል ብይን የሰጠ ቢሆንም ማስረጃዎቹን ማስተባበል ባለመቻሉ ተከላከል በተባለበት ድንጋጌ የጥፋተኝነት ፍርድ ተላልፎበታል፡፡

ዐቃቤ ሕግ የቅጣት ማክበጃ አስተያየት፣ በተከሳሹ በኩል ደግሞ ሰባት የቅጣት ማቅለያ አስተያየት በጽሁፍ ቀርበዋል፡፡የግራ ቀኙን አስተያየት የመረመረው ፍርድ ቤቱ ሰባት የቅጣት ማቅለያ በመያዝ በዕርከን 30 መሰረት ተከሳሹ በ11 አመት ጽኑ እስራትና በ10 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

# ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል ዘርፍ ተኮር ስልጠና ተሰጠ





የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ከፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጋር በመተባበር ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና ለተጠሪ ተቋማት ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች ሥነምግባራዊ አመራርን በማጎልበት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በብሔራዊ ቤተ-መዛግብት እና ቤተ-መፃህፍት አገልግሎት መሰብሰቢያ አዳራሽ ተሰጥቷል:: ሙስናን የመከላከል እና የመግታት ጥረት በአገር አቀፍ ደረጃ ውጤታማ እንዲሆን የተቋሙ እና የተጠሪ ተቋማት አመራሮች እና ሰራተኞች በሥነ-ምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ላይ ግንዛቤ በመያዝ ግልጸኝነትን እና ተጠያቂነትን ተላብሰው እንዲሰሩ ለማስቻል ያለመ ስልጠና መሆኑ ተገልጿል:: በስልጠናው ሙስና እና ብልሹ አሰራር በኢትዮጵያ አብዝቶ መንሠራፋቱንና ለዚህም ምክንያት ከሆኑ ጉዳዮች መካከል በአመራሩ ዘንድ በሥነ-ምግባር ዙሪያ የጠራ ግንዛቤ፣ ስልጠና እና ክትትል አለመኖር፣ የመልካም አስተዳደር ችግሮች በሰዓቱ ምላሽ ያለማግኘት፣ በተቋም ውስጥ ችግሮች በሚከሰቱበት ወቅት የችግሩ መነሻ ምክንያት ከስሩ አለማወቅ ዋነኛ እንደሆኑ ተገልጿል፡፡ ስልጠናው በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የስልጠና ባለሙያ የተሰጠ ሲሆን፥ የተሰጠው ስልጠና በሥነ-ምግባር ምንነት፣ ጽንሰ ሃሳብ፣ መርሆዎች እና አስፈላጊነት ዙሪያ ትኩረት ያደረገ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

በተመሳሳይ መረጃ ለግብርና ሚኒስቴር እንዲሁም ለከተማ እና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት አመራሮች በሥነምግባራዊ አመራር ጽንሰ ሀሳብ እና መገለጫ ባህርያት እንዲሁም ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ያተኮረ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡








## ኤጀንሲው አገልግሎት በመስጠት ሂደት ላይ ያልተገባ ጥቅም የሚያገኙ አካላት ላይ ተጠያቂነትን ለማስፈን እየሰራ ነው



የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ አገልግሎት በመስጠት ሂደት ላይ ያልተገባ ጥቅም የሚያገኙ አካላት ላይ ተጠያቂነትን ለማስፈን እየሰራ መሆኑን ገለፀ። የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ በስድስት ወራት ውስጥ በህገወጥነትና ተጠያቂነት ላይ በተሰሩ ስራዎች ላይ መግለጫ ሰጥቷል። የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮናስ ዓለማየሁ እንደለፁት፤ ኤጀንሲው ከሌብነት የፀዳ አገልግሎት ለመስጠት እየሰራ ነው።

በ6 ወራት ውስጥ በአገልግሎት አሰጣጥ እና በኦዲት ግኝት ላይ ክትትሎች ተደርገዋል። በዚህም የአገልግሎት ኦዲትን በተመለከተ በጠቅላላው 63 ሰዎች ተጠያቂ ሲሆኑ 12 በወንጀል እና 41 በዲሲፕሊን ተጠያቂ ናቸው። ቀሪ 10 የጽ/ቤት አመራሮች ስራን በአግባቡ ባለመምራት ተጠያቂ የሚሆኑ መሆናየውን ገልፀዋል። እንዲሁም በአገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ 47 ባለሙያዎች ተጠያቂ የተደረጉ ሲሆን ከዚህም 34 በከባድ እና ቀላል ዲሲፕሊን እንዲሁም 9 ባለሙያዎች በወንጀል ተከሰዋል ብለዋል። በተጨማሪም 36 ሃሰተኛ ሰነድ ይዘው የተገኙ ተገልጋዮች በህግ ቁጥጥር ስር እንዲውሉ የተደረገ መሆኑን አስታውቀው፤ 4ቱ በወረዳ ጽ/ቤት፣ 34ቱ በኤጀንሲው ዋና መስሪያ ቤት መሆናቸውን ገልፀዋል። ከዚህም ውስጥ 3ቱ ፍርድ ተሰጥተዋል።

## በሐሰተኛ ሰነድ ከባለሀብት 13 ሚሊዮን 888 ሺህ ብር ተቀብሎ የተሰወረው ተጠርጣሪ በቁጥጥር ሥር ዋለ

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ልዩ ቦታ ሴንትራል ማተሚያ ቤት አካባቢ በሐሰተኛ ሠነድ አጭበርብሮ ከባለሀብቱ 13 ሚሊዮን 888 ሺህ ብር ተቀብሎ የተሠወረውን ቱጁባ ቶልቻ ሰንበታ የተባለውን ተጠርጣሪ ለመያዝ ፖሊስ ባደረገው ብርቱ ክትትል በቁጥጥር ሥር አውሎ ምርመራ እያጣራ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ አስታውቋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በዚህ ግለሰብ ተታለልኩ ወይም ተጭበረበርኩ የሚል ማንኛውም ሰው በኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ጠቅላይ መምሪያ ቢሮ ቀርቦ ሪፖርት እንዲያደርግ ተቋሙ ያስታውቃል። ኅብረተሰቡ በተመሳሳይ የወንጀል ተግባር እንዳይታለል ራሱን እንዲጠብቅና በወንጀል መከላከል ውስጥ እያደረገ ያለውን ተሳትፎ የበለጠ አጠናክሮ እንዲቀጥል የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ጥሪውን አቅርቧል።

## ኮሚሽኑ የሙስና ሥጋት ባለባቸው ስድስት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሲያካሄድ የቆየዉን የሙስና መከላከል ጥናት ግኝት ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር አካሄደ

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ሥጋት ባለባቸው ስድስት ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ባካሄደዉ የሙስና መከላከል ጥናት ግኝት ላይ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በይርጋለም ከተማ ምክክር አድርጓል፡፡ ጥናቱ የተካሄደባቸው ስድስቱ ርዕሰ ጉዳዮች በክልሉ በስራ እድል ፈጠራ፣ በገቢ አሰባሰብ ሂደት፣ በሰራተኞች ዝዉዉርና ቅጥር፣ በፋይናንስና ግዢ፣ በትምህርት ቤቶች ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም እንዲሁም የመድሀኒት አቅርቦትና ስርጭት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ያላቸዉን ተጋላጭነት ለይቶ ይፋ ያደረገ ሲሆን፤ ለችግሩም መንስኤ የሆኑትን መለየት መቻሉ ተገልጿል፡፡





የምክክር መድረኩን በንግግር የከፈቱት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የፖለቲካ አቅም ግንባታ ዘርፍ ኃላፊ አቶ አስፋዉ ጎነሳ መንግስት የጀመረዉን የኢኮኖሚ፣ የእድገት፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ጉዞ ለማስቀጠል በየደረጃዉ ካሉ አካላት ጋር ሰፋፊ ስራ እየተከናወነ መቆየቱን ገልፀዋል፡፡ አቶ አስፋዉ አያይዘዉም እንደሀገር ሙስና እና ብልሹ አሰራር በሀገር ላይ የሚያደርሰዉን አሉታዊ ተጽእኖ ለመታገል ሰፊ ስራ እየተከናወነ መሆኑን ገልፀዉ፤ እንደክልላችንም ኮሚቴ በማዋቀር የህዝብንና የመንግስትን ሀብት ለመመዝበር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ጠንካራ ህጋዊ፣ አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ የእርምት እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የሀገር ልማትና እድገት አደናቃፊ የሆነዉን ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በህብረት ልንታገል ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የክልሉ የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ወ/ሮ ዘላለም ለማ በበኩላቸዉ ኮሚሽኑ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ግንዛቤ ከማስጨበጥ ጀምሮ የሙስና ወንጀል ተከስቶ ሲገኝ ጥቆማዎችን መነሻ በማድረግ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የበኩሉን ሲወጣ መቆየቱን ተናግረዋል፡፡ በመድረኩም ሁሉም የሙስና መከላከል ጥናት ግኝቶች ቀርበው ከመድረኩ ተሳታፊዎች ጋር ምክክር በማካሄድ ጥናቱ ከተካሄደባቸው ተቋማት ጋር የተግባራ የዉል ስምምነት ተካሄዷል፡፡

## ከደረሰኝ ጋር ተይይዞ የሚስተዋሉ ችግሮች ላይ አስተማሪ እርምጃ በመውሰድ ህግ ማስከበር ይገባል - ስንታየሁ ወ/ሚካኤል

ያለ ደረሰኝ ህገ ወጥ የንግድ ሥራ በሚያከናውኑ አካላት ላይ አስተማሪ እርምጃ በመውሰድ የክልሉን የገቢ አቅም ማሳደግ እንደሚገባ በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የከተማ ልማት ክላስተር አስተባባሪና የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ስንታየሁ ወ/ሚካኤል ተናገረዋል፡፡ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ገቢዎች ቢሮ የ6 ወራት የስራ አፈፃፀም እና በቀጣይ አቅጣጫዎች ላይ የሚመክር የውይይት መድረክ በቡታጅራ ከተማ ተካሄዷል፡፡

በውይይት መድረኩ ላይ የተገኙት በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የከተማ ልማት ክላስተር አስተባባሪና የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ስንታየሁ ወ/ሚካኤል ልማት የሚፋጠነው ጠንካራ የገቢ አቅም ሲኖር ነው ብለዋል፡፡ የክልሉ መንግስት የገቢ አቅሙን ለማሳደግ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ አሟጦ ለመሰብሰብ እየተሠራ መሆኑንም ገልፀዋል፡፡ ባለፉት 6 ወራት የገቢዎች ሴክተር ያደረገው እንቅስቃሴና ያስገኘው ውጤትም አበረታች መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ቅንጅታዊ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት የገቢ ሥራን ተቋማት በቅንጅት እንዲፈፅሙ ማድረግ እንደሚገባ ያሳሰቡት አቶ ስንታየሁ በዚህም የክልሉን የወጪ ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል አቅም መፍጠር እንደሚቻል አብራርተዋል፡፡ ከታክስ ተገዥነትና ህገ ወጥነት ጋር ተያይዞ ህግ ማስከበር እንደሚገባ አፅንኦት ሰጥተዋል፡፡ በከተሞች በተለይም ደረሰኝ የመስጠት ባህል ከበፊቱም ይልቅ አሁን ላይ እየቀነሰ መምጣቱን ተናግረው ይህን ለማስተካከል ግንዛቤ በመፍጠርና አስተማሪ እርምጃ በመውሰድ ህግ ማስከበር ይገባል ብለዋል፡፡ በዘርፉ የሚስተዋለውን ችግር ለመቅረፍ በቀጣይ የታክስ አገልግሎትን ከንክኪ ነፃ የማድረግና የማዘመን ሥራ በትኩረት የሚሰራ መሆኑን አቶ ስንታየሁ አስታውቀዋል፡፡ በክልሉ ባለፉት ስድስት ወራት 5 ቢሊዮን 895 ሚሊዮን 819 ሺ 999 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 5 ቢሊዮን 43 ሚሊዮን 467 ሺ 461 ብር መሰብሰቡን የገለፁት ደግሞ የክልሉ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘይኔ ቢልካ ናቸው፡፡ ሥራው ቅንጅታዊ አሰራርን የሚጠይቅ በመሆኑ የፊት አመራሩ ተግባሩን በባለቤትነት ወስዶ መንቀሳቀስ መጀመሩ ለተሻለ አፈፃፀም አዎንታዊ አስተዋጽኦ አበርክቷል ብለዋል፡፡ ይሁንና ከክልሉ የወጪ ፍላጎት አንፃር በቀጣይ በልዩ መልኩ መሥራት እንደሚጠይቅ ተናግረዋል፡፡



የሰው ኃይል አለመሟላት፣ የሥነምግባር ችግሮች፣ የጥቅም ግጭትና አድሎአዊነት እንዲሁም በዜጎች ዘንድ ደረሰኝ የመጠየቅና የመቀበል ባህል አለመዳበር ያጋጠሙ ተግዳሮቶች መሆናቸውን አቶ ዘይኔ አብራርተዋል፡፡ በቀጣይ ለህግ ተገዥ ባልሆኑት ላይ ህጋዊ እርምጃ የመውሰድ ሥራ ይከናወናልም ብለዋል፡፡ ከብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ የክልሉን የገቢ አቅም ለማሳደግ የሚደረገውን ጥረት ሁሉም እንዲያግዝ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

## ፀረ-ሙስና


በፌደራል
የሥነምግባር እና
የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
የሚዘጋጅ ወርሃዊ
ጋዜጣ

| | |
|---|---|
| ስልክ | 011552-77-79 |
| ፖ.ሳ.ቁ | 34799 |
| ኢ-ሜይል | FeaccEthiopia2013@et |
| ድረ-ገጽ | www.feacc.gov.et |
| ፌስቡክ | www.facebook.com/feaccOfficial |
| ቴሌግራም | t.me/feacc |
| ትዊተር | www.twitter.com/EthiopiaFeacc |
| ዩቲዩብ | Federal Ethics & Anti-Corruption Commission |

ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች
www.feaccdars.gov.et

ለፌደራል የሥነምግባር
እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
የሙስና ወንጀል ጥቆማ
መስጫ አድራሻዎች

| | |
|---|---|
| ስልክ | 011552 77-92/ 011553-38-52 |
| ሞባይል | 0935947533 |
| ፖ.ሳ.ቁ | 34799 |
| ድረ-ገጽ | www.feacc.gov.et |
| ኢ-ሜይል | CorruptionReportEthiopia@feacc. gov.et |
| ቴሌግራም | t.me/CorruptionPointing |
| ዋትስአፕ | wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1 |


# ርዕሰ-አንቀፅ

## የከተማ መሰረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም ከሙስናና ብልሹ አሰራር የጸዳ መሆኑን ለማረጋገጥ እየተሰራ ያለው ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል!

የኢትዮጵያ መንግስት ከዓለም ባንክ ጋር ባደረገው ስምምነት መሰረት በአሁኑ ወቅት 7 ውጤት ተኮር ፕሮግራሞች በትግበራ ሂደት ላይ ሲሆኑ ሁለት ፕሮግራሞች በዝግጅት ሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ ውጤት ተኮር ፕሮግራሞቹ የኢትዮጵያ መንግስት የየዘርፉን የልማት ፍላጎት ለማገዝ በብድርና በእርዳታ መልክ ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ ፕሮግራሞቹ በተለያዩ የመንግስት ቁልፍ የልማት ዘርፎች ዓላማቻቸውን እንዲያሳኩ ድጋፍ የሚያደርጉ ሲሆን እነዚህንም በጤና፣ በግብርና፣ በትምህርት፣ በውሀና ኢነርጅ፣ በፋይናንስ / ገንዘብ፣ በኢንቨስትምንት/ስራ እድል ፈጠራ እና በከተማና መሰረተ ልማት ዘርፎች ዙሪያ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛል፡፡

የመንግስት የዓለም ባንክ ትብብርና ስምምነት እያደገ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመምጣቱ የፋይናንስ ድጋፉ በዚሁ ልክ እያደገ መጥቷል፡፡ ስለሆነም በእነዚህ ውጤት ተኮር ፕሮግራሞች የፋይናንስ ድጋፉ ስምምነት በህግ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

እነዚህ ውጤት ተኮር ፕሮግራሞች እንደ ሀገር የሥራ አፈጻጸማቸው ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዱ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአመት ሁለት ጊዜ የቬርፊኬሽን/የማረጋገጥ ሥራ እየሠራ ይገኛል፡፡

በዚህ በጀት አመትም በስድስቱ ፕሮጀክቶች የመጀመሪያ የቬርፊኬሽን ሥራ የተሰራ ሲሆን የከተማና መሰረተ ልማት ፕሮጀክት ደግሞ አሁን ላይ በሰፊውና በሚዲያ ሽፋን ጭምር እየተደረገ ይገኛለል፡፡ የዚህ ፕሮጀክት ዓላማ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ከተሞች ተቋማዊ አፈጻጸምን በማሳደግ የከተማ መሰረተ ልማቶችን አገልግሎቶችን እና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማትን ማሻሻል እና ማስቀጠል ነው፡፡

ከዚህ ፕሮጀክትም በከተሞች የእቅድና በጀት ዝግጅት ሂደት የዜጎች ተሳትፎ ማሻሻል፣ በከተማ ደረጃ የገቢ መሰብሰብ ዓቅም መሻሻል፣ የተሻሻለ መሰረተ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥ፣ የተሻሻለ የአካባቢ እና ማህበራዊ አስተዳድር፣ የተጠናከረ የተጠያቂነትና የቁጥጥር ሥርዓቶችን እና መሰል ውጤቶች ይጠበቃሉ፡፡

ይህ ፕሮጀክት እንደ ሀገር በ117 ከተሞች ላይ እየተገበረ ሲሆን በዚህ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እና የሙስና መከላከል ሥራዎች አፈፃፀም ዳሰሳዊ ጥናትና የመስክ ምልከታ መርሃ-ግብር ሥራም በከተሞች ላይ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ፕሮጀክቱ ሰፊ የከተማና መሰረተ ልማት ሥራዎችን የያዘ እንደመሆኑ መጠን አሁን ላይ በልዩ ትኩረት በሚዲያ በታገዘ ሥራ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እና የሙስና መከላከል ሥራዎች አፈፃፀም ዳሰሳዊ ጥናትና የመስክ ምልከታ መርሃ-ግብር እየተሰራ ሲሆን በቀጣይም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

# ቆይታ



**የፀረ-ሙስና ዲጂታል ጋዜጣ የ19ኛ ዕትም እንግዳችን የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ሳሙኤል ካሳሁን ያደረገችውን ቆይታ ለአንባቢያን ይዛ ቀርባለች። መልካም የንባብ ጊዜ.**



**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በቅድሚያ እራስዎን ያስተዋውቁልን;

**አቶ ሳሙኤል፡-** ስሜ ሳሙኤል ካሳሁን ገ/ማርያም ይባላል:: ረዘም ላለ ጊዜ (ለ11 ዓመታት ያክል) በአዳማ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት አገልግያለሁ። ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያንና የፀረ-ሙስና ትግሉን የተቀላቀልኩት በ1999 ዓ.ም. የመጀመሪያ ዓመት የዩኒቨርሲቲ መምህር ሆኘ ነው:: በወቅቱ የነበሩት የድርጅቱ አስተዳዳሪዎች የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከርና በሁሉም ክልል ለማዳረስ ከየክልሉ በበጎ ፍቃደኝነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ጠንካራ ተወካዮችን የቀደመ ታሪካቸውን (background history) በማጥናትና በጥቆማ ሲመለምሉ እኔም የኦሮሚያ ክልል ተወካይ እንድሆን ተመለመልኩኝ ማለት ነው::

ከዛ ጊዜ ጀምሮ ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያንና የፀረ-ሙስና ትግሉን ከማስተማሩ ጎን ለጎን በተለያዩ ሃላፊነቶች ከልቤ ሳገለግልና የፀረ-ሙስና ትግሉን ሳግዝ ቆይቻለሁ። ከሰባት ዓመታት ወዲህ (የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪ ሳለሁ) ጀምሮ ደግሞ የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ የስራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር በመሆን እያገለገልኩ እገኛለሁ። በድምሩ የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያንና የፀረ-ሙስና ትግሉን ከተቀላቀልኩኝ 17 ዓመት ያህል ሆኖኛል ማለት ነው። በነኝህም ዓመታት አቀሜና ከባቢያዊ የስራ ሁኔታው በፈቀደልኝ መጠን የተለያዩ የስነ-ምግባር ግንባታና የፀረ-ሙስና ስራዎችን በሃገር አቀፍ ደረጃ ስመራና ስሰራ ቆይጫለሁ። በመሆኑም በዘመኑ ተዘውታሪ ቃል ራሴን ስገልጽ የጸረ-ሙስና አንቂ (activist) ነኝ እላለሁ::

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ በዋናነት ምንድን ነው የሚሰራው?

**አቶ ሳሙኤል፡-** ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ ከተቋቋመበት ከ1995 ዓ.ም. ጀምሮ ሶስት ዋና ዋና ርዕስ ጉዳዮች ማለትም የሥነ-ምግባር ግንባታ ፣ የፀረ-ሙስና ትግልና መልካም አስተዳደር የማስፈን ስራ ላይ ትኩረቱን አድርጎ ለባለፉት 21 ዓመታት ሲሰራ ቆይቷል፡ ፡ በእነኝህ ወሳኝ ረእስ ጉዳዮች ላይ የሚሰራዉን ስራ ተግባራዊ ለማድረግ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ እስትራቴጅካዊ አምዶችና አቅጣጫዎችን በመንደፍ አቅምና ከባቢያዊ የስራ ሁኔታ በፈቀደ መጠን የተለያዩ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል። የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስቴር ፣ ዶር. አቢይ አህመድ ፣ ወደ ስለጣን ከመጡ በኂላም የተደረጉ ለውጦችን ለምሳሌ የሲቪክ ማህበረሰብ ህጉንና የመሳሰሉትን የህግ ለውጦች ተከትሎ ለ10 ዓመታት ያክል ጨቋኙን የሲቪክ መህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ (አዋጅ ቁ. 621/2002) ተቋቁሞ ለማለፍ ነድፎ ሲጠቀምበት የነበረውን ጊዜያዊ መሸጋገሪያ ስትራቴጅካዊ አቅጣጫ አሻሽሎ አምስት በወቅታዊ የሃገራዊ ሁኔታው ያስሩሉ ያላቸውን አስትራቴጅካዊ አመዶችን በመንደፍና በመከተል የተለያዩ የስነ-ምግባር ግንባታ፣ ከፀረ-ሙስናናከመልካም አስተዳደር ማስፈን ጋር የተያያዙ ስራዎችን በሃገር አቀፍ ደረጃ በመስራት ላይ ይገኛል።

ስትራቴጅክ አምዶቹን ለማንሳት ያክል የመጀመሪያው ተቋማት ጠንካራና ሃላፊነት የሚሰማቸው እንዲሆኑ መስራት፤ በስነ-ምግባር የታነጸ ማህበረሰብን እንዲኖረን መስራት፣ ግልጽ የመንግስት ግዢ (public procurement) እንዲኖር መስራት ፣ የማህበረሰብ ተጠያቂነት እንዲሰፍን መስራት ፤ እና በሀገራችን ብሎም በቀጠናችን ጠንካራ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ እንዲኖር መስራት።

እነኝህን ስትራቴጅክ አምዶች መሰረት ያደረጉ የተለያዩ ተግባራትን ለምሳሌ የጥናትና ምርምር፣ የግንዛቤ ማስረጽ ፣ የጸረ-ሙስና ንቅናቄዎችንና ጥምረቶችን ማደራጀት፣ የህግ ምክርና ድጋፍ አገልግሎት፣ የፖሊሲ ውይይቶችና ውትወታዎች የመሳሰሉትን በመንደፍ የተለያዩ ስራዎችን በሀገር አቀፍ ደረጃ በትጋትና በቁርጠኝነት እየሰራ ይገኛል።

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** ትረንስፓረንሲ ኢትዮጵያ በተጓዘባቸው አመታት የገጠሙት ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?

**አቶ ሳሙኤል፡-** ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ ባሳለፋቸው 21 ዓመታት ውስጥ ልክ እንደ ሌሎቹ የሰብዓዊ መብት ፣ የመልካምና አስተዳደርና የዴሞክራሲ ግንባታና የመሳሰሉት ተግባራት ላይ ተሰማርተው የሚሰሩት ሀገር በቀል የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ያጋጠሚቸውን ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮች እየተጋፈጠ ነው እዚህ የደረሰው።

እንደሚታወቀው የኛ ሃገር ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ለሚሰሩ የሀገር በቀል የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች አስቻይ ከባቢያዊ እውነታ አለው ለማለት የሚቻልበት ደረጃ ላይ አየደለንም፡ ከሁሉም በላይ ግን ምርጫ 97ን ተመርኩዞ 2002 ዓ.ም. ላይ የወጣው የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ከሁሉ በላይ እኛንም መሰል ሀገር በቀል ድርጅቶችን ከሁሉ በላይ የጎዳ አደገኛ ተግዳሮት ሆኖ አልፏል።

ይህ አዋጅ ብዙ ሀገር በቀል ድርጅቶችን ያጠፋ እንደሆነ በጥናት ተረጋግጧል። የተረፍነው ጥቂቶቹ ድርጅቶች በጠንካራ የጠቅላላ ጉባኤና የቦርድ አባሎቻችንና በያቅጣጫው የፀረ-ሙስና ትግሉን ወደውና ፈቅደው በተቀላቀሉትና በተፈለጉበት ቦታ ተልእኳቸውን ያለማመንታት፣ የለመሰለቸትና መድከም ባግባቡ በሚወጡት የበጎ ፈቃደኞቻችን ትጋት ነው። ሆኖም ይህ ጨቋኝ አዋጅ ያደረሰብን ኢኮኖሚያዊ ድቀት ለአስር አመታት ያህል ተግባራችንን ባግባቡ እንዳንወጣና ህልውናችን ላይ ብቻ አተኩረን

እንድነጨነቅ ትልቅ ተግዳሮት ሆኖን አልፏል። ዶር አቢይ ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ ጨቋኝ አዋጅ ቢሻሻልም ቅሉ ብዙዎቻችን ከላይ የጠቀስናቸው ጉዳዮች ላይ የምንሰራ ተቋማት እስካሁን ድረስ የቀደመው አዋጅ ሀንጎቨር ወይም ትራውማ ያለቀቀን መሆኑ ብዙ ማሳያ አለ። በርግጥ በአዲሱም አመራር ከህግ ለውጥ በስተቀር ብዙ መሰራት ያለባቸው የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶችን የማጠናከር ስራ ተሰርቷል ብየ አላምንም።

ምናልባት በተለያዩ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮች ሊሳበብ ቢችልም የሃገር በቀል ተቋማትን የማጠናከር ስራው እኩል ትኩረት ተሰጥቶ ቢሰራበት ምናልባት በሃገራችን በተደጋጋሚ ለሚስተዋለው ፖለቲካዊና ማህበራዊ ቀውስም መፍትሄ ሊሆን እንደሚችል አምናለሁ።

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ሙስናና ብልሹ አሰራሮች በየጊዜው እየጨመሩ የሚስተዋልበት ወቅት ላይ ነው ያለነው። ይህን ከመከላከል አኳያ የትኛው የህብረተሰብ ክፍል በሃላፊነት ይመለከተዋል ብለው ያስባሉ?

አቶ ሳሙዔል፡- እውነት ነው ሙስናና ብልሹ አሰራር ከመቸውም ጊዝ በላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚስተዋልበት ጊዜ ላይ ነው ያለነው። ይህንን አደገኛና ሃገርንና ማህበረሰብን አሰነካክሎ የሚያስቀር አካሄድ ለማዳን እና ለመከላከል የሁላችንንም የባለ ድርሻ አካላት (የመንግስትን ፣ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶችን ፣ የመገናኛ ብዘሁሃንን ፣ የእምነት ተቋማትን ፣ የትምህርት ተቋማትን ፣ የፍትህና የዴሞክራሲ ተቋማትን፣ ወሀተረፈ) ርብርብ ይሻል። ይህ ትግል ሁሉንም የባለ ድርሻ አካላትና የማህበረሰቡን ርብርብ ቢፈልግም በዋናነት ግን መንግስት ያንበሳውን ድርሻ ወስዶ የፀረ-ሙስና ትግሉን በበላይነት መምራት አለበት ብየ አምናለሁ።

በዚህም ረገድ ከመንግስት በዋናነት ያስፈልገዋል ብየ የማምነው ፖለቲካዊ ፈቀደኝነትና ቁርጠኝነት፣ political will and determination፣ ነው። ስለዚህ ከመንግስት ሙስናን በመዋጋት ረገድ ከመቸውም ጊዜ በላይ የተጠናከረ ፖለቲካዊ ፈቃድ ወይም መነሳሳትና ቁርጠኝነትን፣ political will and determination፣ አሳድጎ ወጥ በሆንና አይነኬነትን ባስወገደ መልኩ የፀረ-ሙስና ትግሉን ሊመራ የገባል። እንደኔ እምነት ይህ ትግል የነብር ጭራን እንደመያዝ ነው። የነብር ጭራን አይዙትም ከያዙም አይለቁትም እንዲሉ የህ ትግል ወጣ ገባን እና ፈራ ተባን አያፈልግም። በዚህ ረገድ ከመቸውም ጊዜ በላይ መንግስት ወጥ በሆነ መልኩ ህግን የማስተግበር ስራና የዴሞክራሲ ተቋማትን (እንደ የፌደራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን) ፣ ልክ እነ ኢንዶኔዥያ እንዳደረጉት፣ የማጠናከር ስራም መስራት አለበት።

ነገራችን ኢትዮጵያ ህግን ባግባቡና ከፖለቲካ ነጻ በሆነ ሁኔታ የማስተግበር (enforcement) ችግር እንጅ የህግ ችግር አለባት ብየ አላምንም። ነገር ግን ህግ ውጤተማ እንዲሆን የቀጣቱ አስተማሪነት በጥንቃቄ የተጠና መሆን ስላለበት ህጋችንንም መለስ በሎ አስተማሪነቱን ማጥናት ተገቢ በሚሆንበት ጊዜ መንግስ ትኩረተ ሰጥቶ ቢያስጠናም ተገቢ ነው እላለሁ የህገ መዩም የቅጣት አስተማሪነት ከቦታ ቦታ ከሃገር ሀገር ስለሚለያይ። ለማነኛውም እንደኔ እምነትና በፀረ-ሙስና ትግሉ ዉጤታማ እንደሆኑ ሃገራት የፀረ-ሙስና ትግሉን መንግስት የአንበሳውን ድርሻ ወስዶ ከመቸውም ጊዜ በላይ የፖለቲካ ቁርጠኝነቱን አሳድጎ ወጥና አየነኬነትን ባስወገደ መልኩ መምራት አለመት። ሌሎች የባለ ድርሻ አካላትም የሄንን ገዳይ ነቀርሳ በማስወገድ ስገድ ከመቸውም ጊዝ በላይ የበኩላችንን ርብርብ ማድረግ ይኖርብናል።

> ይህንን አደገኛ ሃገርንና ማህበረሰብን አሰነካክሎ የሚያስቀር አካሄድ ለማዳን እና ለመከላከል የሁላችንንም የባለድርሻ አካላት ርብርብ ይሻል።

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- የመልካም አስተዳደርና የሙስና ችግር በዚህ ፍጥነት ከቀጠለ የሃገሪቷ የወደፊት እጣ ፋንታ ምን የሚሆን ይመስልዎታል?

አቶ ሳሙዔል፡- የህን ወሳኝ ጥያቄ ከብዙ ነገር አንጻር ለማብራራት ብወድም ለአንባብያን ይቀል ዘንድ በጭሩ ሃሳቤን ለመገለጽ ፣ የህ ችግር አሁን ባለበት አካሄድ ከቀጠለ የሃገራችን እጣ ፍንታ ልክ እንደ ሌሎች ፈርሰዋል እንደሚባሉ የአለም ሃገራ ለምሳሌ እንደ ሶሪያ መፍረስ፣ መበተን፣ ስደትና እና ቸነፈር የቅርበ ጊዜ ሃቅ ሊሆን እንደሚችል አልጠራጠርም። ከስር እየገዘገዙ ዛፉ አይወድቅም ኢትዮጵያ አተፈርስም በሚለው ብሂል አላምንም። ብዙ ጥናቶችና ምልከታዎች እንደሚያሳዩት ለብዙ ሀገራት ውድቀት ዋና ምክንያት ሙስና እንዲሁም ብልሹ ግልጽነትና ተጠያቂነት የጎደለው አሰራር ነው።

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ እንደ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል መረጃ መሰረት ስንተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች?

አቶ ሳሙኤል፡- ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል በየዓመቱ 180 ሀገራትን በማካተት በገለልተኛ አጥኝዎች የሚየጠናው Corruption Perception Index (CPI) እንደሚያሳየው ሀገራችን ኢትዮጵያ በዚህ ዓመት ማለትም እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2023 አቆጣጠር 98ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። በነገራችን ላይ ጠቅላይ ሚኒስቴር አቢይ አህመድ ወደ ስልጣን በመጡበት ዓመት 114ኛ ነበረን። አሳቸው በመጡ በአመቱ ብዙ ተስፋ የሚሰጡ የለውጥ እንቅስቃሴዎች ለምሳሌ የተለያዩ አፋኝና ጨቋኝ የሚባሉ ህጎች (የሲቪል ማህበረሰብ፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የሽብር፣ ወዘተ) መሻሻልና የመሳሰሉት ለወጦች ተስፋ የሰጡ ይመስለኛል የመረጃ ምንጮቹን አረዳድ ቀይረው ሀገራችን ኢትዮጵያ ብዙ ሀገራትንና ተቋማትን ባስገረመ ሁኔታ በ18 ደረጃዎች አሻሽላ 96 ደረጃ ላይ ተቀምጣ ነበር።

ከዛ በኋላ በነበሩት ሁለት ተከታታይ አመታትም መሻሻሎችን አሳይታ 94ኛና 87ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣ ነበር። ከዛ በኃላ ባሉት ሁለት አመታት ደግሞ (ከትግረዩ ጦርነት በኂላ) ወደ ቁልቁል መሄድ ጀምረን አምና 95ኛ ዘንድሮ ድግሞ 98ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጠናል። በዚህ አካሄድ ክቀጠልን ከዱሮው ደረጃችንም በታች ልናሽቆለቁል እንደምንችል መገመቱ ከባድ አይሆንም።

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- በጸረ-ሙስና ትግሉ እንደ መንግስት ምን መሰራት አለበት ይላሉ?

አቶ ሳሙኤል፡- የዚህን ጥያቄ መልስ ከሞላ ጎደል አራተኛው ጥያቄ ላይ መልሸዋለሁ። እንዲሁ ጠቅለል አድርጎ ለመመለስ በዋናነት መንግስት ያንበሳውን ድርሻ ወስዶ የጸረ-ሙስና ትግሉን መምራት አለበት። በዚህ ረገድ ከመቸውም ጊዝ በላይ ከመንግስት የፖለቲካዊ ፍላጎት ወይም ፈቃድና ቁርጠኝነትን መጨመር ግዴታ ነው ብየ አምናለሁ።

ስለዚህ መንግስተ ከመቸውም ጊዜ በላይ ቁርጠኝነቱን ጠብቆ አድልዎንና አይነኬነትን (impunity) አስወግዶ ወጥ በሆነ መልኩ የፀረ-ሙስና ትግሉን መምራት የጠበቅበታል።

በዚህ ረገድ እንደ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ ፍትህ ሚኒስቴር እና ፖሊስ የመሳሰል

የፍትህና የዴሞክራሲ ተቋማትን ማጠናከርና ነጻና ገለልተኛ እንዲሆኑ ማደረግ የፀረ-ሙስና ትግረሉን ለማሳለጥ ይጠቅማል:: በተጨማሪ በፀረ-ሙስና ዙሪያ የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ እንደ ትራንስፓረንሲ ያሉ ተቋማትን ማገዝና ማጠናከር በሎም አስቻይ ህጎችንና ከባቢያዊ ሁኔታዎችን መፍጠር አሁንም የፀረ-ሙስና ትግሉን ያሳልጣል::

ከዚህ በተጨማሪ የህግ የበላይነትን ማስፈን ከመንግስት ይጠበቃል:: በዚህ ረገድ ህግን ያለ አድልዎ ማስፈጸምና አስተማሪነቱም ላይ ተደጋጋሚ ጥናት በማስጠናት ህጉን አስተማሪ እንዲሆን ማድረግ የህግና የቅጣት አስተማሪንት ከቦታ ቦታና ከሃገር ሃገር ስለሚለያይ ለምሳሌ ከህንድ የተወሰደው ህግና የቅጣት ፕሮሲጀር በኛ ሃገር መስራት አለመስራቱን በጥናት ማረጋግጥህግ አውጭው፣ አስተርጓሚና አስፈጻሚው ተናበው እንዲሰሩ ማድረግ፡፡ በፓርላማው ጠንካራ በነጻነትና በገለልተኝነት የሚሰራ የጸረ-ሙስና ኮሚቴ እንዲኖር ማድረግ:: የመገናኛ ብዙሃንንና የሲቪክ ማህበረሰብ በፀረ-ሙስና ዙሪያ የሚኖራቸውን ሚና ማጠናከር፡፡ ወዘተ

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** ግልጽነትና ተጠያቂነት አለ ይላሉ; ከሌለ ምን መደረግ አለበት?

**አቶ ሳሙዔል፡-** ግልጽነትና ተጠያቂነት በሚጠበቀው መጠን አለ ብየ አላምንም:: በዚህም ረገድ መንግስት ያነበሳውን ድርሻ ወስዶ ተቋማት ግልጽነትና ተጠያቂነት እ ን ዲ ያ ዳ ብ ሩ ና እ ሴ ታ ቸ ው እንዲያደረጉፖሊሲዎችን ህጎችንና መመሪያዎችን በማረቀቅ በማጽደቅና በማስተግበር ረገድ ከፍተኛ ሚና ሊኖረው ይገባል፡፡ ሌላውን በ4ኛወና በ7ኛው ጥያቄ ስር ከሞላ ጎደል ነካክቸዋልሁ፡፡

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- የስነ-ምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን በጸረ-ሙስና ትግሉ ሲያግዙ ለነበሩ ተቋማት እውቅናና ማበረታቻ ሰጥቷል፡፡ እዉቅና በማግኘትዎ ምን ተሰማዎ? በቀጣይስ የበለጠ ለመስራት ዝግጅትዎ ምን ይመስላል?

**አቶ ሳሙኤል፡-** በቅድሚያ ድካማችንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በየጊዜው እውቅና እየሰጠን ያለውን በመንግስት ወገን ሆኖ የሚያየንን የሚያግዘንንና የሚያበረታታንን የኢፌዴሪ የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን ይህን አጋጣሚ ተጠቅሜ በራሴና በተቋሜ ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ ስም ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

ብዙ መስዋእትነት የከፈልንበት ድካማችንና ሃገራዊ አበርክቷችን እውቅና ስላገኘ በጣም ደስ ብሎኛል:: ይህ ትግል ብዙ መስዋእትነትን የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን መስዋእትነታችንንና አበርክቷችንን ከመንግስት ወገን ሆኖ የሚያይ አካል ስላለንም የአጋርነትና የአብሮነት ስሜት በውስጣችን የሚያጭረው ደስታ ለቀጣይ የስራ እቅዳችን ማቀጣጠያ ነዳጅ እንደሚሆነን አልጠራጠርም፡፡

ይህ እውቅና አብሮ የሚሰጠን አደራም ስላለው አደራችንን ለመወጣት በቀጣይ ተግተን እንደምንሰራ ከወዲሁ ላረጋግጥ እወዳለሁ፡፡ አሁንም ውሃ የሚቋጥርና በፀረ-ሙስና ትግሉ ዙሪያ በጎ ተጽእኖን ይፈጥራሉ ለውጥ ያመጣሉ የምንላቸውን ተግባራት ለመስራት ተዘጋጅተናል:: በዚህም ረገድ የኮሚሽኑ አብሮነት ትግላችንን እንደሚያሳልጠው አልጠራጠርም፡፡

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በመጨረሻ ማለት የሚፈልጉት ያልተነሱ ሃሳቦች ካሉ እድል ልስጥዎት?

አቶ ሳሙዔል፡- ብዙውን ሃሳቤን ከላይ ባሉት ጥያቄዎች ስር ስለገለጽኩ የምጨምረው ነገር የለኝም፡፡ ራሳችንን ለመግለጽ ለሰጣችሁን እድል እንዲሁም ለሰጣችሁን እውቅናና ላሳያችሁን አብሮነት በራሴና በድርጅቴ ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ ስም **ከልብ**

***አመሰግናለሁ፡፡***



# ሳይቃጠል በቅጠል

## የመስመር የቁማር ውርርዶች በወጣት ማህበረሰብ የፈጠረው አሉታዊ ተፅእኖ እና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሰደው አወንታዊ እርምጃ!

በሐረጎት አብረሃ

በፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የስነምግባርና ፀረ-ሙስና አስፈጻሚዎች መሪ ስራ አስፈፃሚ

በዓለማችን ያለው ህብረተሰብ በየቀኑ ራሱን ለማዝናናት፣ ጤንነት ለመጠበቅ፣ ማህበረሰባዊ ግንኙነትን ለማጠናከር ብሎ የሚፈጥራቸው የተለያዩ የመዝናኛ አይነቶች ቁጥራቸው ቀላል አይደሉም፡፡ ከዚህ ውስጥ የስፖርት መዝናኛ አንዱ ሲሆን፣ በዓለማችን እንደ ትልቅ ኢንዳስትሪ የሚወሰድ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ይሁን በየሀገሩ የሚከናወኑ በሺህ የሚቆጠሩ የስፖርት መዝናኛዎች እንዳሉ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

የስፖርት ውድድሮች እንደ ጥሩ መዝናኛ የሚወሰዱ ቢሆንም አልፎ አልፎ አሉታዊ ተፅእኖ የሚፍጥሩበት ሁኔታ አለ፡፡ በተለይም በቅርብ ግዜ በግፍ እየተስፋፋ ያሉ ፈጠራ ላይ የተመሰረቱ የመስመር (online) የስፖርት ውርርዶች በአንድ ማህብረሰብ ግንኙት፣ ስነ ልቦና፣ ባህል፣ ኢኮኖሚ እና ጤና ላይ ተፅእኖ እየፈጠሩ እንዳሉ መረጃዎች የሚያሳዩ ሲሆን በሀገራችን ኢትዮጵያም በስፋት ቅሬታ እየተነሳባቸው ይገኛል፡፡ ለዛሬ የፅሁፌ መነሻ የትኩረት ነጥብ ሆኖ እንዲነሳ የፈልግኩቱም በቅርብ ጊዜ ሀገራችን የወረሩት በኦንላይ አፕሊኬሽን ተመስርተው የሚከናወኑ የቁማር እና የስፖርት ውርርድዶች በሀገራችን ወጣት ማህበረሰብ ላይ የፈጠሩትን ተፅእኖ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

ቁማር ማለት ሁለት ተጫዎቾች ወይም ተወዳዳሪዎች ወይም ተወራራጆች አንዳቸው ካተረፈ (ካሸነፈ) ከከሰረው (ከተሸነፈው) ላይ ገንዘብ እንዲወስድ ቅድመ መስፈርት



በሚቀመጥለት ውድድርና ጨዋታ በማካሄድ የሚከናወን ጨዋታ ነው ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡ ፡ ፡ቁማር መጫወት በአንድ አንድ ሀገራት እንደ ጥሩ ጊዜ ማሳለፍያ፣ መዝናኛ/ መደሰቻ ተድርጎ ሲወሰድ፥ በአንድ አንድ ቦታ ደግሞ ቁማር በአብዛኛው በሌሎች ኪሳራ ገንዘብ ማግበስበስ ስለሆነ የተወገዘ እንደ ወንጀል የሚቆጥርበት ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ በመፅሃፍ ቅዱስ (ሉቃስ 12:15 “ከመጎምጀትም ሁሉ ተጠበቁ” ይላል፡፡

ይህ ማለት አንድን ሰው ቁማር እንዲጫወት የሚገፋፋው መጎምጀት ወይም ስግብግብነት ስለሆነ ወደ መጎምጀት የሚወሰዱ ነገሮች ከማከናወን መታቀብ እንዳለባቸው ይመክራል፡፡ በተመሳሳይ በእስልምና ሀይማኖት ቁማር እርም ነው፤ በቁማር ምክንያት የሚከሰት ወንጀልና ጉዳት በርሱ ከሚገኝ ጥቅም እጅግ የገዘፈ መሆኑን የእስልምና ታልቁ መፅሀፍ ቁርኣን በግልፅ አስቀምጧል፡፡ በአንፃሩ ቁማር ሕጋዊ በሆነ መንገድ እስከተደረገ ድረስ ምንም አይነት ጉዳት የሌለው እና አንደ መዝናኛ ሊወሰድ እና የገቢ ምንጭ ሆኖ ሊያገልግል እንደሚችል የሚገልፁ አሉ፡፡ ለዚህ እንደምክንያት የሚያነሱት በህግ እስከተፈቀደ ድረስ ቁማር ለሕዝብ ጥቅም የሚውሉ ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም እንደ ገቢ ማሰባሰብያ ሆኖ ሊወሰድ እንደሚችል የህግ መከራከሪያ ያነሳሉ፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያም ከውርርዶችና የቁማር ጨዋታዎች ጋር በተያያዘ በ1996 የወጣውን የኢፌድሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 789(1) ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡ ፡ በድንጋጌው መሰረት ማንኛውም ሰው አግባብ ካለው ባለስልጣን ፈቃድ ሳያገኝ ትርፍ ለማግኘት ሲል ሎተሪዎችን፣ እንደ ሙያ የተያዙ የውርርድ ጨዋታዎችን ያቋቋመ፤ ወይም ትርፍ ለማግኘት ሲል ያለፍቃድ በአደባባይ ወይም ለህዝብ ክፍት በሆነ ቦታ ወይም ለመሰበሳቢያ በተዘጋጀ ክበብ የቁማር ጨዋታን፣ ወይም ውርርዶችን ወይም በመንግስት የተከለከሉ ማናቸውም ሌሎች የእድል ጨዋታዎችን አቋቁሞ የነገደ ወይም እንደዚህ ባለ ጨዋታ ወይም ውርርድ የተሳተፈ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ አግባብነት ያለውን ሕግ ወይም ደንብ ወይም መመሪያን የጣሰ እንደሆነ በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን ገልፆ በአዋጁ አንቀጽ 789 (2) ላይ ለህዝብ ጥቅም ወይም ለበጎ አድራጎት ዓላማ ሲባል በሕግ አግባብ የሚቋቋሙ ሎተሪዎችና ውርርዶች የሚያስቀጡ አይደሉም በሚል ያስመጣል፡፡

የብሄራዊ ሎተሪ አስተዳደር ተቋም ለማቋቋም የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና እና መመሪያዎች እንደሚያሳዩት የስፖርት ውድድር ሎተሪ አንዱ የሎተሪ አይነት መሆኑን ገልፆ የመስመር የውርርድ ስፖርት ማካሄድ እንደሚቻል ይገልፃል፡፡ በአጠቃላይ የስፖርት ውርርድ ጨምሮ የተለያዩ ቁማሮች ለመቆጣጠር የሚያስችል ሁሉ የሕግ ማዕቀፎች ቢኖሩም የሕግ ማዕቀፉ ወቅታዊ ከማድረግ እና በህግ ተፈቅደው የሚከናወኑ እንደ የስፓርት ውርርድ አይነቶች ከመፈቀዳቸው በፊት በማህበረሰብ ላይ ሊፈጥሩት የሚችሉት አወንታዊ እና አሉታዊ ተፅእኖ በዝርዝር ገምገሞ እና ጥናት አድርጎ ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ክፍተቶች እንዳሉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

### ቁማር አመራጭ የገቢ ምንጭ ተደርጎ ይወሰዳልን?

ቁማር በአብዛኛው አሉታዊ ተፅእኖ የሚበዛ ቢሆንም ህጋዊ መሰረት ይዞ ከተከናወነ እና ማህበረሰባዊ ትስስሮች እና እሰቴቶችን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን ክትትል እና ቁጥጥር ከተደረገበት የተለያዩ ጥቅሞች እንዳሉት ይገለፃል፡፡ የቁማር ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ዓቅሙ እሰከ 35 ቢልዮን ዶላር ሊደርስ እንደሚችል ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በታላቋ ሀገር አሜሪካ እንደ ላስቬጋስ ከተማ እንዲሁም የቻይና ልዩ ግዛት የሆነችው ማካዎን ዋና የኢኮኖሚ መሰረታቸው ከቁማር የሚገኝ ገቢ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንደ አሜሪካ ያሉ አገሮች ቁማር እንደ የገቢ ምንጭ ብቻ ሳይሆን የስራ እድል እና የገቢ ምንጭ፣ ብሄራዊ የታክስ ገቢ ለማሳደግ፣ የቱሪዝም እና ለቱሪስቶች መዝናኛ ሆኖ እንዲያገልግል በማድረግ ትልቅ ሚና እንዳለው ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ያም ሆኖ በአውስትራሊያ በካዚኖ መልክ ወደ 290,000 እንዲሁም በአሜሪካ ወደ 7.9 ሚልዮን የሚጠጉ አዋቂዎች ልማደኛ ቁማርተኞች እንዲሁም

በአውስትራሊያ በዓመት ብቻ ከ3 ቢልዮን ዶላር በላይ የሚበልጥ ኪሰራ እንደሚያደርስም ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ ያለው የገቢ መጠን ግልፅ መረጃች ባይኖርም የብሄራዊ ሎተሪ አስተዳደር ውርርዶች ጨምሮ የተፈቀዱ ሎቶሪዎች በጣም ጥቂት ሰዎች ሀብታም በማድረግ ብዙሃኑ ደግሞ ለከፍተኛ ኪስራ የታደረጉ ሰዎች እንዳሉ ጥቆማዎች አሉ፡፡ በአጠቃላይ ቁማር ለተወሰኑ ሰዎች የተወሰነ ገቢ በማሳደግ ሚና ይኖረዋል ተብሎ የሚገመት ቢሆንም በአህገራችን በተለይም በቅርቡ በስፋት እየተስፋፋ የመጣውን የስፓርት ውርርድ ዘርፈ ብዙ ተፅእኖ እየፈጠረ እንዳለ ግን የማይካድ ሀቅ ነው፡፡

## በኢንተርኔት ድህረ ገጾች የሚካሄዱ የውርርድ እና የቁማር ጨዋታዎች እና የፈጠሩት ስጋት

ከላይ ለማንሳት እንደሞከረኩት በቅርብ ጊዜ ስሙ እየገነነ የመጣው የቁማር አይነት አንዱ በኢንተርኔት አማካኝነት የሚከናወኑ የመስመር (Online) ውርርዶች ናቸው፡፡ ብዙ አይነት የመስመር ቁማሮች ቢኖሩም የመስመር ላይ የካሲኖ ጨዋታዎች፣ የስፖርት ውርርድ፣ የፈረስ እሽቅድምድምና ዕለታዊ ምናባዊ ስፖርቶች ወ.ዘ.ተ በጥቂቱ የሚነሱ ናቸው፡፡ በመስመር ወይም ኦንላይን የሚካሄዱ ቁማሮች ሁለት አይነት ገፅታ አላቸው፡፡ አንደኛው ትክክለኛ ውድድሮች በማየት የሚካሄድ የስፓርት ውድድሮች ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ምናባዊ ውድድር በማድረግ ሊከናወን የሚችል ነው፡፡ ለምሳሌ በየሳምንቱ የሚካሄዱ የእንግሊዝ ፕሪመርሊግ ጨዋታዎች ውጤት የመገመት ቁማር ትክክልኛ ውድድሮች ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ቁማር ሲሆን በአንፃሩ ፕላይስቴሽን መሰረት አድርጎ የሚከናወን ቁማር ምናባዊ ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

የመስመር ቁማሮች ከሚመለከታቸው ፍቃድ በመውሰድ ወይም በኢንተርኔት አማካኝነት ከጎግል ስቶር በማውረድ ሊከናወኑ የሚችሉ ናቸው፡፡ በአደጉ አገሮች እነዚህ ቁማሮች ትክክለኛ ፈቃድ ለተሰጣቸው ወይም የመስመር ላይ የቁማር ምርቶች እንዲሸጡ የተፈቀደላቸው የቁማር መተግበሪያዎች (አፕሊኬሽኖች) አማካኝነት ስራ ላይ በአግባቡ እና ለተፈቀደለት ዓላማ የሚልውበት አግባብ ሲኖር፥ ባላደጉት አገሮች በዘፈቀደ ጥቅሙ እና ጉዳቱ በአግባቡ ተሰልቶ ስራ ላይ የሚውልበት አግባብ በጣም አነሰተኛ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የጎንዮች ጉዳት ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን ሳይረጋገጥ ስራ ላይ የሚውሉ ቁማሮች ከፍተኛ የሆነ ግላዊ እና ማህበረሰባዊ ቀውስ ያስከትላሉ፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው በመዲናችን አዲስ አበባ እና በክልሎች ላይ የሚሰተዋለው የየኦንላይ ስፖርታዊ ዉርርድ (ቤቲንግ) አንዱ ሲሆን በእጅጉ ከፍተኛ ማህበረሰባዊ ቀውስ እየፈጠረ ስለመሆኑ ከህ/ሰቡ በስፋት ይስተዋላል፡፡

የስፖርት ውርርድ (Betting Game) ለመቆመር ብለው ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎች፣ በየሰፈሩ የሚገኙ ስራ ያላቸው እና የሌላቸው ወጣቶች ውሎ አደራቸው እነዚህ የውርርድ ስፓርት ላይ ተጠምደው የሚገኙበት ሁኔታ አለ፡፡ የስፓርት ውድድሮችን በማቋመር ገንዘብ ለማግኘት ብለው በየቀኑ ለዚህ ተብለው የተከፈቱ የንግድ ሱቆች የትየሌለ ናቸው፡፡ እኔ በምኖርበት አካባቢ እና ለስራ ተዘዋውሬ በታዝኩባቸው ክልሎችና ከተማ አስተዳድሮች ይህ አይነት የስፓርት ውድድር ቁማር በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍቶ ለማየት ተችሏል፡፡

ከህብረተሰብ መረጃ ለመረዳት እንደተቻለው በተለይም እድሚያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ተማሪዎችና ህፃናት በዚህ ሱስ በስፋት ተጠምደው ይታያሉ፡፡ ተማሪ የወጣቱን ህይወት በማጎሳቆል በትምህርት እንዲሰነፍ፣ ደካማ የስራ ባህል እንዲኖረው፤ ሲያድግም ሰርቶ ከመብላት በአቋራጭ የመበልፀግ አስተሳስብ እንዲያዳብር ያደርጋል፡፡ ቢዘህ ውስጥ የገቡ ወጣቶች ሱሳቸውን ለማስታገስ ብለው ወደ ስርቆት የመግባት፣ ለትምህርት የተሰጣቸው የትምህርት መሳሪያ ጭምር እስከ መሸጥ ድረስ የደረሰ ተፅእኖ እየፈጠረ ስለመሆኑና ይህ ሱስ የሚያጠቃው ወጣቶች ብቻ ሳይሆን አዋቂዎች ጭምር በመሆኑ በቤተሰብ እና ማህብረሰባዊ ግንኙኝት ላይ ጫና እያሳደረ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በዚህ ውስጥ የገቡ ሰዎች የቆጠቡት ገንዛባቸው በአንዴ በማጥፋት ድሃ የሆኑ እንዳሉም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ወደ ሌላ ብድር መግባት፣ በደረሰው ኪሰራ ወደ ፀብ እና ድብደባ ውስጥ መግባት በአጠቃላይ ራስን እስከማጥፋት የደረሰ ጉዳት እንዳስከተለ ከተለያዩ የህብረተሰብ አካላት የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወሰደው አወንታዊ እርምጃ

ቁማር እና የተለያዩ ውርርዶች ከሚያስገኙት ጥቅም ይልቅ ጉዳታቸው ያመዝናል፡፡ በቅርብ በመዲናችን በሆነችው አዲስ አበባ የሚታየው ችግር አንዱ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ እንጂ ችግሩ በሁሉም አካባቢዎች አለ፡፡ በተለያየ ደረጃ ያሉ አመራሮች ለችግሩ ትኩረት ስጠተው መፍትሄ መስጠት አለባቸው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክብርት ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አበቤ የስፖርት ውርርድ በማህበሰብ እና ወጣቶች ያደረሰውን ተፅእኖ በመረዳት የስፖርት የውርርድ ፍቃድ ወስደው ስራው ሲያከናውኑ የነበሩ የተለያዩ የንግድ ሱቆች ፈጣን እርምጃ በመውሰድ ለጊዜውም ቢሆንም እንዲታሸግ ማደረጋቸው ወቅታዊና ተገቢ ውሳኔ በመሆኑ አስተዳደሩን ማመስገን ይገባል፡፡ በቀጣይም ችግሩ ለመፍታት የብሄራዊ ሎተሪ አስተዳደር ጨምሮ የሚለከታቸው አካላት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት የሚከተሉት ተግባራዊ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡፡

አንደኛና ዋነኛ ጉዳይ የመስመር ስፖርታዊ ውድድሮች የሚመሩበት ግልፅና ጠንካራ ፓሊሲ እና ህግ ማውጣት ያስፈልጋል፡፡ የሚወጡ ህጎች እና ፓሊሲ ለገቢ ሳይሆን ቅድሚያ የግለሰብ እና ማህብረሰብ ግንኙነት እና እሴቶች ቅድሚያ ሊሰጡ ይገባል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶች ሊሰራ የሚገባው ጉዳይ ከአጠቃላይ ፓሊሲ እና ህግ የሚመነጭ ቢሆንም የቁማር እና ስፖርታዊ ውድድሮች ለማስተዋወቅ ተብሎ በየመንገዱ በመኪና ሳይቀር ጠቃሚነቱን የሚሰበክበት አግባብ አለ፡፡ ለዚህ ማሳያ እንዲሆን ‹‹… በግምት ብቻ በአጭር ጊዜ በቀላሉ ሕይወትዎን የሚቀይሩበት ታላቁ ዘዴ›› በውርርዱ እስከ 350 ሺህ ብር ያግኙ! የሚል ማስታወቅያ በመኪና በማስነገር በክልሎች የማስታዋወቅ ስራ በማከናወን ለዓመታት በረሃ ለበረሃ ዞሮ ላቡን አፍስሶ ያጠራቀመውን አንጡራ ሀብቱን እንዲያጣ የሚያደረግ መሆኑን ያገኙኃቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ስራው ፍቃድ አግኝቶ ይቀጥል ከተባለም ልክ የሲጋራ እና የቢራ ውጤቶች እንደተከለከለው የውርርድ ማስታወቂያዎች ሊከለከሉ እና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ በዚህ የተሰማሩ የንግድ ተቋማት ከ18 በታች ዕድሜ ያላቸው ወጣቶች በስፖርታዊ ውርርዶች እንዳይሳተፉ የሚገልፅ ማስታወቅያ በየግድግዳቸው የሚለጥፉበት አግባብ ቢኖርም በተግባር ግን ቁጥጥር ሲያደርጉ አይታይም፡፡

በሦስተኛ ደረጃ የብሄራዊ ሎቶሪ አስተዳደር እና የሚመለከታቸው የፀጥታ አካላት የውርርድ ስፓርት እንዲቀጥል ከተወሰነ አፈፃፀሙን በየግዜው በመከታተል አተገባበሩ ላይ ችግር ያለበት የንግድ ተቋም ወይም ካምፓኒ ጠንከር ያለ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ እያንዳንዱ ቤተሰብም ልጆቻቸውን በመቆጣጠር እና ከእንደዚህ አይነት አልባሌ ቦታዎ እንዲርቅ የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው፡

በአጠቃላይ የቁማር እና የውርርድ ይዘት ያላቸው የስፓርት መዝናኛ ተብለው በሀገራችን በገፍ እየተስፋፋ ያሉ ተግባራት ከተቻለ በዘላቂነት መከልከል፣ ካልተቻለ ደግሞ ከፍተኛ ቁጥጥር እየተደረገበት የሀገር እና የአብዛኛው ማህበረሰብ ጥቅም ባስቀደመ መልኩ ሊከናወኑ ይገባል፡፡

……………………………

# ከሙስና ምርመራ ማህደር

በተጭበረበረ የባንክ ስቴትመንት የኢንቨስትመንት መሬት ለመረከብ ሲንቀሳቀስ የነበረ ግለሰብ በህግ ቁጥጥር ስር ውሏል፡፡ በአሪ ዞን በቅባት እህል ዘርፍ የኢንቨስትመንት መሬት ለመረከብ ዋልዕሽት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በሚል ስያሜ የሚንቀሳቀሰው ማህበር ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ተጠርጣሪ አቶ ግዛው ነጋሽ ለኢንቨስትመንት የሚያስፈልገውን ካፒታል 30 በመቶ ማለትም 32 ሚሊዮን 246 ሺህ 340 ብር እንዲሁም ከባንክ ብድር 70 በመቶ ማለትም 75 ሚሊዮን 246 ሺህ 460 ብር በጠቅላላ 107 ሚሊዮን 492 ሺህ 800 ካፒታል ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡ በቀድሞ የደቡብ ኦሞ ዞን ካቢኔ ማህበሩ የጠየቀው 10 ሺህ ሄክታር ቢሆንም ባቀረበው ካፒታል 400 ሄክታር እንዲሰጣቸው ውሳኔ ተላልፎ ለቀድሞ የደቡብ ብሔር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ጭምር መረጃው እንዲደርስ መደረጉን የአሪ ዞን ኢንቨስትመንት መምሪያ ኃላፊ አቶ ፍቅረስላሴ ጀማል በሰጡት መግለጫ አስታውሰዋል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች ግለሰቡ በወቅቱ የሚጠበቅበትን አሟልቶ ሳይረከብ ዘግይቶ በአሁን ወቅት መሬቱ ወደ ልማት መግባት እንዳለበት አዲሱ የአሪ ዞን ኢንቨስትመንት መምሪያ ውሳኔ መተላለፉን የመመሪያው ኃላፊ ገልፀዋል፡፡ ተጠርጣሪው ግለሰብ መሬቱን ለመረከብ ሲል ከአዲስ አበባ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጎፋ ካምፕ ቅርንጫፍ የድርሻውን 30 በመቶውን ቆጥቢያለሁ በሚል 48 ሚሊዮን 650 ሺህ ብር የባንክ ስቴትመንት ለአሪ ዞን ኢንቨስትመንት መምሪያ ያቀርባል፡፡ ዋልዕሽት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥራ አስኪያጅ ያቀረበውን የባንክ ስቴትመንት ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ መምሪያው በአቅራቢያ ለሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ህጋዊ ደብዳቤ ይፅፋል፡፡

ንግድ ባንኩም ይህንን መነሻ በማድረግ ሲያጣራ በግለሰቡ አካውንት የተጠቀሰው የገንዘብ መጠን አለመኖሩን ያረጋግጣል፡፡ በዚህም ተጠርጣሪው ግለሰብ የባንክ ስቴትመንት አመጣሁ ወዳለው አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መረጃው እንዲደርስ ሲደረግ ባንኩም በግለሰቡ የተከፈተ አካውንት መኖሩንና በአካውንቱ ገንዘብ አለመኖሩን ዳግም ያረጋግጣል፡፡ በዚህ ብቻ ሳያበቃ ግለሰቡ ከአዲስ አበባ ከተጠቀሰው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጎፋ ካምፕ ስቴትመንት ተሰጥቶኛል ብሎ ያቀረበው ከባንኩ ያልተሰጠ ከመሆኑም ባለፈ ሐሰተኛ ሰነድ መሆኑም ጭምር ይረጋገጣል፡፡ ይህንን ጉዳይ በጥንቃቄ ሲያጣራ የነበረው የአሪ ዞን ኢንቨስትመንት መምሪያ መረጃዎችን አደራጅቶ ለአሪ ዞን አስተዳደርና ፖሊስ መምሪያ ያሳውቃል፡፡

ግለሰቡ ጉዳዩን ለማስፈፀም የአሪ ዞን ኢንቨስትመንት መምሪያ በተገኘበት በፀጥታ አካላት በህግ ቁጥጥር ስር እንዲውል መደረጉን የመምሪያው ኃላፊ አቶ ፍቅረስላሴ ጀማል ለደቡብ ሬዲዮና ቴሌቭዥን ድርጅት ጂንካ ቅርንጫፍ በሰጡት መግለጫ አስታውቀዋል፡፡ የዞኑ ዋና አስተዳዳር ጉዳዩን በመደገፍ ላበረከተው አስተዋፅኦ አቶ ፍቅረስላሴ በመምሪያው ስም አመስግኗል፡፡ ኃላፊነት በጎደላቸው አካላት በሚደረግ ህገ ወጥ እንቅስቃሴ በርካታ የሀገር ሀብት ሳይለማ ከመቅረቱ ባሻገር ብልሹ አሠራር በሀገሪቱ እንዲንሰራፋ ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ ሁሉም አካል ጉዳዩን ሊያወግዝ ይገባል ሲል መልዕክት አስተላልፏል፡፡

የአሪ ዞን ፖሊስ መምሪያ የማህብረሰብ አቀፍ ወንጀል መከላከል ዲቪዥን ኃላፊ ምክትል ኢንስፔክተር ሽብሩ አማሬ እንደገለፁት ተጠርጣሪው ግለሰብ በአሁን ወቅት በህግ ቁጥጥር ስር ውሎ ምርመራ እየተደረገበት እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡ የማጣራቱ ሂደት ሲጠናቀቅ ክስ እንዲመሠረት ይደረጋል ብለዋል፡፡ በዞኑ ኢንቨስትመንት መምሪያ በኩል የተደረገው ተግባር የሚደነቅ ነው ሲሉም ምክትል ኢንስፔክተር ተናግረዋል፡፡

በሌላ የሙስና ወንጀል መረጃ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ ጊዜ ቀጠሮ ችሎት በሙስና ወንጀል የተጠረጠረው የፍርድ ቤት ዳኛ ላይ ክስ የመመስረቻ ጊዜ ለዐቃቤ ሕግ ሰጠ፡፡ ተጠርጣሪው የአዲስ አበባ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዳኛ እና የፍርድ ቤቱ የኢንስፔክሽን ኃላፊ የሆነው ተስፋዬ ደረጄ፤ ከዚህ በፊት በሙስና ወንጀል ተከሶ የነበረ ሀብተማርያም ገ/መስቀል የተባለ ግለሰብን ጉዳይ የሚመለከቱ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኞች አብረውት እንደተማሩና እንደሚያውቃቸው በመጥቀስ እንዲሁም አንደኛውን ዳኛ "የስራ አለቃዬ ስለሚያውቀው ነጻ አወጣሃለው" በማለት በማግባባት የሙስና ገንዘብ ተቀብሏል ተብሎ ተጠርጥሮ በቁጥጥር ስር ውሎ ምርመራ ሲከናወንበት ነበር፡፡ ምርመራውን ሲያከናውን የነበረው የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን መርማሪ ፖሊስ የምርመራ ስራውን አጠናቆ መዝገቡን ለዐቃቤ ሕግ ማስረከቡን አስታውቋል፡፡

የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ የምርመራ መዝገቡን ተመልክቶ ክስ ለመመስረት እንዲያስችለው በወ/መ/ስ/ህ/ ቁጥር 109/1 መሰረት የ15 ቀን ክስ የመመስረቻ ጊዜ እንዲሰጠው ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ተጠርጣሪው በበኩሉ የተጠረጠረበት የወንጀል ተግባር በሙስና ወንጀል ጉዳይ ሊታይ አይገባም በማለት በመከራከር ፍርድ ቤቱ የዋስትና መብቱን እንዲያከብርለት ጠይቋል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ ግለሰቡ የተጠረጠረበት የወንጀል ድርጊት ዋስትናን የሚያስከለክልና ከ10 ዓመት በላይ ሊያስቀጣ የሚችል በከባድ የሙስና ድንጋጌ የሚያስከስስ መሆኑን በመጥቀስ የተጠርጣሪው የዋስትና ጥያቄ ውድቅ እንዲደግ ጠይቋል፡፡ የግራ ቀኝ ክርክሩን የተከታተለው ጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ የተጠርጣሪዎችን የዋስትና ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ለዐቃቤ ሕግ ክስ የመመስረቻ ጊዜ መስጠት አስፈላጊነትን በማመን 15 ቀን የክስ መመስረቻ ጊዜ ፈቅዷል፡፡

በተያያዘ የሙስና ወንጀል መረጃ የአ/አ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ የቀድሞ የፕሮቶኮል ዳይሬክተር እነ ኤልቤቴል ሀብቴ ላይ በተጠረጠሩበት የሙስና ወንጀል የክስ ለመመስረት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ጊዜ ቀጠሮ ችሎት ለዐቃቤ ሕግ 15 ቀን ሰጠ፡፡ ተጠርጣሪዎቹ የአ/አ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ የቀድሞ የፕሮቶኮል ዳይሬክተር ኤልቤቴል ሀብቴ፣ የፍትህ ሚኒስቴር ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ ሀብት አስተዳደር ዳይሬክተር ፍቅሩ ኦላና እንዲሁም በግል ስራ ይተዳደራሉ የተባሉት ቅዱስ መስፍን፣ አማኑኤል መስፍንና ተክሌ ከቡ የተባሉ ግለሰቦች ናቸው፡፡

ተጠርጣሪዎቹ ከ17 ነጋዴዎች ከውጭ ሀገር እቃ ለማስመጣት በሚል ከተወሰደ ከ46 ሚሊየን ብር በላይ ገንዘብ ጋር ተያይዞ ስልጣንን ያለአግባብ በመገልገል እና ከማታለል ተግባር ጋር ተያይዞ በወንጀል ተጠርጥረው ምርመራ ሲከናወንባቸው ቆይቷል፡፡

የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን መርማሪ በተጠርጣሪዎቹ ላይ ሲያከናውን የቆየውን የምርመራ ስራ ማጠናቀቁንና የምርመራ መዝገቡን ለዐቃቤ ሕግ ማስረከቡን አስታውቋል። የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ በበኩሉ የምርመራ መዝገቡን ተመልክቶ ለመወሰንና ክስ ለመመስረት እንዲያስችለው በወ/መ/ስ/ህ/ ቁጥር 109/1 መሰረት የ15 ቀን ክስ የመመስረቻ ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቋል። የተጠርጣሪዎቹ ጠበቆች የዐቃቤ ሕግ የክስ መመስረቻ ጥያቄን በመቃወም የተጠረጠሩበት ወንጀል ተራ መሆኑን ጠቅሰው የዋስትና መብታቸው እንዲፈቀድ ጠይቀዋል።

ዐቃቤ ሕግ በተፈፀመው የወንጀል ድርጊት ከ46 ሚሊየን ብር በላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑን በመጥቀስ ዋስትናን በሚያስነፍግ እና ከ10 ዓመት በላይ በሚያስቀጣ በከባድ የሙስና ድንጋጌ ሊከሰሱ እንደሚችሉ ገልጾ፣ የዋስትና ጥያቄው ውድቅ እንዲደረግለት ፍርድ ቤቱን ጠይቋል። የግራ ቀኝ ክርክሩን የተከታተለው ጊዜ ቀጠሮ ችሎቱ የዋስትና ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ለዐቃቤ ሕግ ክስ የመመስረቻ ጊዜ መስጠት አስፈላጊነትን በማመን 15 ቀናትን ፈቅዷል።

በሌላ የሙስና ወንጀል መረጃ ከሶማሌ ክልል ተፈናቃይ ነን በማለት በሀሰተኛ ሰነድ በመንግስት ላይ ከ8 ሚሊየን ብር በላይ ጉዳት አድርሰዋል የተባሉ 20 ግለሰቦች እንዲከላከሉ የኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት ብይን ሰጠ። የክልሉ ፍትህ ቢሮ የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በነሃሴ ወር 2015 ዓ.ም ሶስት ክሶችን ካቀረበባቸው 50 ተከሳሾች መካከል ብርሃኑ ግርማ፣ ደረጀ ጌታቸው፣ ዱቦ ፉፋ፣ ሙሳ አብዲን ጨምሮ ሌሎች የሚገኙበት ሲሆን በቁጥጥር ስር ውለው ፍርድ ቤት የቀረቡት ግን 21 ብቻ ናቸው። ዐቃቤ ሕግ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 ንዑስ ቁጥር 1 ሀ እና አንቀጽ 696 (ሐ) ስር የተመለከተውን እንዲሁም የሙስና አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 4 ንዑስ ቁጥር 4፣ አንቀጽ 23 (2.3) እና አንቀጽ 32 (3.2) ላይ የተመላከተውን ድንጋጌ ተላልፈዋል በማለት የክስ ዝርዝር አቅርቦባቸዋል።

በቀረበው በአንደኛው ክስ ላይ እደተመላከተው ከ1ኛ እስከ 5ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተከሳሾች ከሶማሌ ክልል በግጭት ምክንያት ከኦሮሚያ ክልል አዋሳኝ አካባቢ የተፈናቀሉ 1 ሺህ 854 ዜጎች የተፈናቃይ ኮሚቴ ሆነው ሲሰሩ ከአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በተጻፈ የእርዳታና ድጎማ ደብዳቤ መነሻ የአ/አ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በወቅቱ በኮዬ ፌጬ አካባቢ ለተፈናቃዮች ቤት እንዲሰራ በወሰነው ውሳኔ መሰረት ለተፈናቃዮች የድጋፍና ድጎማ ስራ ሲጀምር በጥር 16 ቀን 2010 ዓ.ም

ተፈናቃይ ያልሆኑ ግለሰቦች በሀሰተኛ ጊዜያዊ መታወቂያና ሰነድ ዝርዝር እንዲካተት አድርገዋል በሚል ተጠቅሷል። በተለይም ተፈናቃይ ዜጎችን የመደጎምና የመኖሪያ ቤት የመስጠት ሂደት ውስጥ ከ5ኛ እስከ 30ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች ተፈናቃይ ነን በማለት ሀሰተኛ የተፈናቃይ ጊዜያዊ መታወቂያና የተለያዩ ሀሰተኛ ሰነዶችን በማቅረብ በማጭበርበር በእርዳታ ድጎማው ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉ በክሱ ዝርዝር ተመላክቷል።

በሌላኛው ክስ ደግሞ ከ31ኛ እስከ 50ኛ ተራ ቁጥር የተካተቱ ተከሳሾች በተለያየ ጊዜ ሀሰተኛ የተፈናቃይ መታወቂያዎችን እና ከሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ካንፓስ የተሰጠ የሚመስሉ ሀሰተኛ ሰነዶችን በተለያዩ ስም ዝርዝሮች በማቅረብ ተሳትፎ ያላቸው ተከሳሾች መኖራቸው ተጠቅሷል። በዚህ መልኩ ተከሳሾቹ በጥቅም በመመሳጠር ተፈናቃይ ሳይሆኑ ነን በማለት እና ተፈናቃይ እንደሆኑ የሚገልጹ ቅጾችን በመሙላት እና በማስሞላት ጭምር ባደረጉት ተሳትፎ በኮዬ ፌጬ አካባቢ እያንዳንዳቸው 705 ሺህ 225 ብር ከ04 ሳንቲም የሚገመት መኖሪያ ቤት በመውሰድ እንዲሁም 19 ሺህ 600 ብር ድጎማ እያንዳንዳቸው በተለያየ ጊዜ በመቀበል በተፈጸመ የማጭበርበር የሙስና ወንጀል ድርጊት በመንግስት ላይ 8 ሚሊየን 697 ሺህ 876 ብር ከ08 ሳንቲም ጉዳት አድርሰዋል በማለት ዐቃቤ ሕግ የተከሳሾቹን ሚና ጠቅሶ ክስ መስርቶባቸው ነበር።

ይሁንና ፍርድ ቤት የቀረቡና ክሱ እንዲደርሳቸው የተደረጉ 21 ተከሳሾች በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጊት አለመፈጸማቸውን ጠቅሰው የዕምነት ክህደት ቃላቸውን በመስጠታቸው ዐቃቤ ሕግ 14 የሰው ምስክሮችና ለወንጀሉ መፈፀም ያስረዳሉ ያላቸውን የተቋማት እና የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል።

ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ከመረመረ በኋላ 20 ተከሳሾች በቀረቡባቸው የክስ ድንጋጌዎች እንዲከላከሉ ዛሬ በዋለው ችሎት ብይን ሰጥቷል። በክስ መዝገቡ ላይ በ21ኛ ተራ ቁጥር ላይ የተጠቀሰው ተከሳሽ ግን በነጻ ተሰናብቷል። ፍርድ ቤቱ የሁለተኛ ክስ ጭብጥ ከአንደኛ ክስ ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ጠቅሶ ሁለተኛ ክስ ከአንደኛው ክስ ጋር እንዲጠቃለል አድርጓል። ተከላከሉ የተባሉ 20 ተከሳሾችን በሚመለከት የመከላከያ ማስረጃ ካላቸው ለመጠባበቅ ለየካቲት 11 ቀን 2016 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል።

በሌላ የሙስና ወንጀል መረጃ አትሌት ድሪባ መርጋን ጨምሮ 3 ግለሰቦች ሀሰተኛ ሰነድ አዘጋጅቶ በመገልገል የሙስና ወንጀል ክስ ተመሰረተባቸው። ክሱ የተመሰረተው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው። ተከሳሾቹ አትሌት ድሪባ መርጋ እጅጉ በግል ስራ የሚተዳደሩት ወ/ሮ መንበረ አበበ ገብረጻዲቅ እና አቶ ስዩም አሰፋ ወንድማገኝ ናቸው።

የፍትህ ሚኒስቴር የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ በተከሳሾቹ ላይ የተሳትፎ ደረጃ ጠቅሶ ተደራራቢ ክስ አቅርቦባቸዋል። በዚህም በአንደኛው ክስ በአትሌት ድሪባ ላይ ብቻ በቀረበው ክስ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 ንዑስ ቁጥር 3 ስር የተመላከተውን ድንጋጌ ተላልፏል የሚል ነው።

ተከሳሹ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ 1ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር በሆነውና በስራ አስኪያጅነት የሚተዳደረውን የናይስ ሪል ስቴት ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሆነውንና በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 08 ስር የሚገኘውን 4 ሺህ 972 ካሬ ሜትር ይዞታን ተመሳስለው የተዘጋጁ ሀሰተኛ ሰነዶችን ማለትም በመጋቢት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ከሚመለከተው ተቋም እንደተሰጠ በማስመሰል የተዘጋጀ ሀሰተኛ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለሶስተኛ ወገን ለሽያጭ ማቅረቡን ጠቅሶ ዐቃቤ ሕግ በክሱ አስፍሯል። በተጨማሪም አትሌት ድሪባ የተባለው ተከሳሽ በውል ቁጥር 2036/2012 ዓ.ም ደግሞ በውል ሰጭ የቂርቆስ ክፍለ ከተማ መሬት ዝግጅት እና ማስተላለፍ ዘርፍ እና በውል ተቀባይ ናይስ ሪል ስቴት ኃ/የተ/የግ/ማህበር መካከል የተፈረመ በማስመሰል የተዘጋጀ ሀሰተኛ የሊዝ ውል፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የተሰጠ በጥር 26 ቀን 2015 ዓ.ም በኮድ ቁጥር 2929/2929/2015 የሊዝ ውልን በማሻሻል እንደላከ በማስመሰል የተዘጋጀ ሀሰተኛ የሊዝ ውል ለሽያጭ አቅርቧል በማለት ዐቃቤ ሕግ በክሱ አመላክቷል።

በተጨማሪም ተከሳሹ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ውክልና ባልሰጠበት ሁኔታ ላይ በህዳር 5 ቀን 2016 ዓ.ም ለ1ኛ ተከሳሽ ይዞታውን በሽያጭ እስከ ማስተላለፍ ድረስ እንዲያስተዳድር ውክልና እንደሰጠች ተደርጎ የተዘጋጀ ሀሰተኛ የውክልና ሰነድ ማቅረቡን በክሱ ላይ አመላክቷል።

በአጠቃላይ 1ኛ ተከሳሽ በታህሳስ 4 ቀን 2016 ዓ.ም በይዞታው ላይ የተጠቀሱ ሀሰተኛ ሰነዶችን ትክክለኛ አስመስሎ ይዞ በማቅረብ ይዞታውን በ700 ሚልየን ብር ለመሸጥ ሲደራደር የተያዘ መሆኑን ጠቅሶ ዐቃቤ ሕግ በሀሰተኛ መንግስታዊ ሰነድ መገልገል የሙስና ወንጀል ክስ አቅርቦበታል። በ2ኛና በ3ኛ ተከሳሾች ላይ ብቻ በቀረበው ክስ ደግሞ ተከሳሾቹ በ1996 ዓ.ም በወጣው የኢፌድሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 ንዑስ

# ማንኛውንም ጉዳይ አስፈጽማለሁ በማለት ህብረተሰቡን በማጭበርበር ገንዘብ ሲቀበል የነበረ ግለሰብ በቁጥጥር ስር መዋሉ ተገለፀ



በወላይታ ሶዶ ከተማ በፋና ወምባ ቀበሌ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት የቤቶች ልማት ዘርፍ ባለሙያ አቶ ሄኖክ ቴጋ ማንኛውንም ጉዳይ አስፈጽማለሁ በማለት ህብረተሰቡን በማጭበርበር ገንዘብ ሲቀበል በቁጥጥር ሥር መዋሉን የከተማው ፖሊስ አስታወቀ:: በህግ ቁጥጥር ስር የዋለው ግለሰብ የማዘጋጃ ቤቱ ስራ አስኪያጅ ጓደኛዬ ነው፥ ጉዳያችሁን እኔ አስፈጽማለሁ በማለት ህብረተሰቡን ሲያጭበረብርና ገንዘብ ሲቀበል እንደነበረ ፖሊስ ገልጿል::ግለሰቡ በተለያዩ ጊዜያት ከባለጉዳዮች የቀበሌ ቤት እኔ እሰጣለሁ፣ የትኛውንም ሥራዎችን እኔ አስፈጽማለሁ፣ የማዘጋጃ ቤቱ ስራ አስኪያጅ ጓደኛዬ ነው በማለት ገንዘብ ሲቀበል እንደነበር የተገለፀ ሲሆን፥ ግለሰቡ የተለመደ የማጭበርበር ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ተይዟል::

የወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል በልዩ ትኩረት እየሰራ በመሆኑ ማንኛውም ባለጉዳይ አገልግሎት ለማግኘት ወደ ተቋማት ሲሄድ እጅ መንሻ፣ ጉቦ እና ያልተገባ ጥቅም የሚጠይቁ ግለሰቦች ሲያጋጥም ለህግ አካላት ጥቆማ እንዲሰጡ ጥሪ አቅርባል:: ስለሆነም በከተማው ፖሊስ የስልክ መስመር 04655510146 በመደወል ሙሰኞችንና መሰል ድርጊት ፈፃሚዎችን በማንኛውንም ሰዓት ጥቆማ እንዲሰጡ የወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደር አሳስቧል::

## ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በማዘጋጀት ወንጀል የተከሰሰው የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ሰራተኛ በእስራት ተቀጣ

ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃን በማዘጋጀት ወንጀል የተከሰሰው የሻንቡ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ሰራተኛ በ8 ዓመት ከ5 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት ውሳኔ አሳለፈ:: የኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ የሙስና ጉዳዮች ዐቃቤ ሕግ የሙስና አዋጅ 881/2007 ድንጋጌን መተላለፉን ጠቅሶ ሶሬሳ አፋታ ላይ ክስ መስርቶበታል:: ተከሳሹ በጥር 17 ቀን 2015 ዓ.ም በሻንቡ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ውስጥ የተማሪዎች ምዝገባ ኦፊሰር ሆኖ ሲሰራ በተቋሙ አመራሮች ፊርማ የተዘጋጀ የሚመስል ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎችና የሙያ ማረጋገጪያ ምስክር ወረቀቶችን በ34 ግለሰቦች ስም አዘጋጅቶ የተገኘ መሆኑ በክሱ ዝርዝር ላይ ተጠቅሷል::

በዚህ መልኩ የቀረበበት ክስ ለተከሳሹ እንዲደርስ ከተደረገ በኋላ ተከሳሹ ወንጀሉን አለመፈጸሙን ጠቅሶ የዕምነት ክህደት ቃሉን ሰጥቷል:: ይህን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን የሰውና የሰነድ ማስረጃን መርምሮ በተከሰሰበት ድንጋጌ እንዲከላከል ብይን የሰጠ ቢሆንም ተከሳሹ መከላከል ባለመቻሉ የጥፋተኝነት ፍርድ ተላልፎበታል:: ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኝ የቅጣት አስተያየትን ከመረመረ በኋላ ተከሳሹን ጥፋተኛ በተባለበት ድንጋጌ በ8 ዓመት ከ5 ወራት ጽኑ እስራትና በ1 ሺህ ብር ገንዘብ እንዲቀጣ ወስኗል::

## ምርመራ ማህደር……


ቁጥር 1 (ሀ) እና የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 ንዑስ ቁጥር 1 (ሀ) ስር የተመለከተውን ተላልፈዋል የሚል ነው::

በዚህም 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሳቸው ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስበው በ1ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር በሆነው እና በስራ አስኪያጅነት የሚተዳደረው ናይስ ሪል እስቴት ኃ/የተ/የግ/ማህበር ይዞታ የሆነውንና በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 08 ስር የሚገኘውን 4 ሺህ 972 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ ተመሳስሎ የተሰራ ሀሰተኛ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ፣ የሊዝ ውልና የውክልና ሰነድ ያዘጋጁ መሆኑን ጠቅሶ ሀሰተኛ መንግስታዊ ሰነድ ማዘጋጀት የሙስና ወንጀል ክስ ዐቃቤ ሕግ አቅርቦባቸዋል:: 3ኛ ክስ ደግሞ በ2ኛ ተከሳሽ ላይ ብቻ የቀረበ ሲሆን ይኸውም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 390 ንዑስ ቁጥር 1 ስር የተመለከተውን መተላለፍ የሚል ክስ ቀርቦባታል::

በዚህም በታህሳስ 4 ቀን በ 2016 ዓ.ም በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 08 ልዩ ቦታው አረንጓዴ ሰፈር ተብሎ ከሚታወቀው ቦታ አካባቢ በሚገኘው የስራ ቦታዋ ውስጥ በፍርድ ቤት ትእዛዝ መሰረት በተደረገ ብርበራ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በልደታ ክ/ከተማ ትምህርትና ስልጠና ጽ/ቤት የዕውቀት ለህብረት የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት የተማሪዎች ካርድ እና በትምህርት ሚኒስቴር አባይ የመጀመርያ ደረጃ ት/ቤት የተማሪ ውጤት መግለጫ ካርድ የተገኘባት በመሆኑ የሐሰት ስራ ለመፈጸም የሚያገለግሉ መሳርያዎችና መስርያዎች ይዞ መገኘት ወንጀል ተከሳለች:: በዚህ መልኩ የቀረበባቸው ክስ ዝርዝር በችሎት እንዲደርሳቸው ተደርጓል::

◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇◇

# ኪነ-ጥበብ



## ሰው በእጁ እየሄደ

ሰው ሰው ሁን ተብሎ ሲፈጠር በአምላኩ፣
ሁሉን እንዲገዛ ሲሰጠው በልኩ፣
አድርጎለት ነበር ሁልን በየመልኩ፡፡
ግን የአምላክ ፍጥረቱ ከተፈጥሮው ወርዶ፣
ደንብና ስርዓት ህግጋትን ንዶ፣
እውነትን በጣጥሶ ውሸትን ሰንዶ፣
ተፈጥሮው ተዛባ ሰው በእጁ እየሄደ…
ሰው በእጁ ተራምዶ፡፡
ክቡሩን ተፈጥሮ አምላኩ ሲፈጥረው፣
በህይወት ለመኖር ጥረህ ብላ ሲለው፣
የምድርን አራዊት ሁሉን እንዲገዛው፣
ሰው በእጁ እየሄደ እግሩን አዋረደው፡፡
አምላኩ ሲፈጥረው እጅ ሲያበጅለት ፣
እንዲለወጥ ነበር ሰርቶ እንዲበላበት፣
ግን ሰው ተንኮለኛው ግብሩን አገላበጠ፣
የተሰጠውን እጅ ምንነቱን ሽጠ ፣
የተሰጠውን ግብር የእጁን ሥራ ትቶት፣
ባልተሠጠው ግብሩ ሰው በጁ ሄደበት፡፡

ሰውነቱ ቀርቶ ከተፈጥሮው ወጥቶ፣
ስራውን ለመስራት በእግሩ መሄድ ትቶ፣
በእጁ የሚራመድ ውሸትን አንግቶ፣
ከተፈጥሮው አልፎ ውሸትን አግዝፎ፣
ከሰውነት ወርዶ ስብናውን ገፎ ፣
በአቋራጩ መንገድ እጁን ተደግፎ፣
እግረኛ ይቀድማል በእጅ መንገድ አልፎ፡፡
እናም ሰው ሆይ ተወው በእጅ መሄድህን፣
ሥራን ለማስፈጸም ጉቦ መስጠትህን፣
አጭሩን ጉዳና የስህተት ጉዞህን፣
የስህተትን መንገድ መረማመጃህን፣
በእጅ የምትሄድበት የውሸት ሥራህን፡፡
ሥራህ ለማስፈጸም ተጠቅመህ ደላላ፣
ገንዘብክን አድርገህ ለጊዜዓዊ መላ፣
በስህተትህ መንገድ ከአምላክ አትጣላ፣
በፈቀደልህ ሂድ በእጅ መሄዱን ጥላ፣
በእውነተኛው መንገድ ጥረህ ግረህ ብላ፡፡

የዚህ ግጥም ጭብጥ ወይም ሊተላለፍ የተፈለገው ሀሳብ የሰው ልጅ ጥሮና ግሮ እንዲበላ በአምላኩ ትዕዛዝ ተሰጥቶት እያለ አበቋራጭ መንገድና የመደለያ ገንዘብ ጉቦ እየሰጠ በውሸት በዙዎችን የሚበድል እንደሆነና ይህ ድርጊት ጥሩ እንዳልሆነ አውቆ ሰርቶ መብላት እንዳለበት ምክረ-ሀሳብ የሚሰጥ ነው፡፡

ከያብባል አዲስ

# መልካም ዜጋ

## የፖሊስ አባሉ ወደ ባንክ አካወንታቸው በስህተት የገባን 45 ሺህ 200 ብር ተመላሽ አደረጉ



በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሀድያ ዞን የጊምቢቹ ከተማ ፖሊስ ባልደረባ ዋና ሳጂን መስፍን አለሙ ወደ ባንክ አካውንታቸው በስህተት የገባን 45 ሺህ 200 ብር ተመላሽ አደረጉ። ገንዘቡ የልፋታቸው ዉጤት እንዳልሆነ የተረዱት ዋና ሳጅን መስፍን ወደ ጊምቢቹ ከተማ አቢሲንያ ባንክ ቅርንጫፍ ሄደዉ በማመልከት ለባለቤቱ እንዲመለስ ማድረጋቸው ከከተማው አስተዳደር መንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ከዚህ መልካም ዜጋ የምንማረው ግለሰቡ መልካም ሥነምግባርን የተላበሰ እና የራስ ያልሆነን ሀብትና ንብረት መውሰድ ተገቢ እንዳልሆነ ነው። እንዲህ አይነቱ ዜጋ ለሌሎች አርዓያና ተምሳሌት የሚሆን ነው። በተለይም ደግሞ የህግ የበላይነትን ለማስከበር ከሚሰሩ የህግ አካላት እንዲህ አይነት መልካም ዜጋና ለሌሎች አርዓያ የሚሆን ሰው ማግኘት ለሀገር ጉልህ የሆነ ጠቀሜታ አለው። ሥለሆነም እንዲህ አይነት መልካም ሥነምግባር ያላቸው ግለሰቦችን አርዓያና ተምሳሌት በማድረግ ሁላችንም የበኩላችንን ድርሻ መወጣት አለብን። በዚህ ክፍልም ይህ ግለሰብ ለሌሎች ምሳሌ ይሆናል በማለት ልናቀርበው ወደድን።



# ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ያወጣው የ2023 የሀገራት ሙስና ስጋት መረጃ




በደረጃው መሰረት ዴንማርክ ከ100 ነጥብ 90 በማግኘት ለስድስተኛ ተከታታይ አመት ዝቅተኛ ወይንም ምንም ሙስና የማይታይባት ሀገር ሆናለች። ፊንላንድ እና ኒውዝላንድ ደግሞ በ87 እና 85 ነጥብ ሁለተኛ እና ሶስተኛ ደረጃን ይዘዋል።

ኖርዌይ፣ ሲንጋፖር፣ ስዊድን፣ ስዊዘርላንድ፣ ኔዘርላንድስ፣ ጀርመን እና ሉግዘንበርግ እስከ 10ኛ ያለውን ደረጃ መያዛቸውንም የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል የ2023 ሪፖርት ያመላክታል።

ካለፈው አመት በአንድ ነጥብ ዝቅ ያለችው ኢትዮጵያም በ37 ነጥብ 98ኛ ደረጃን ይዛለች። ሶማሊያ በ2023ም ሙስና የተንሰራፋባት ሀገር በመሆን በ11 ነጥብ የመጨረሻውን ደረጃ (180ኛ) ይዛለች።

ደቡብ ሱዳን፣ ሶሪያ፣ ቬንዙዌላ፣ የመን፣ እና ሰሜን ኮሪያም ሙስና የተንሰራፋባቸው ሀገራት ተብለው በደረጃው ግርጌ ላይ ተቀምጠዋል።